ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

# ፀረ-ሙስና

ፀረ–ሙስና ቅጽ 1 ቁጥር 7 መጋቢት 2015 ዓ.ም





## የፀረ-ሙስና ኮሚቴ መቋቋሙን ተከትሎ ጩኸት በርክቷል፥ ይህም አቁሙ የሚል ነው፤ ኮሚቴው ስራውን አጠናክሮ ይቀጥላል፥ ሙስና በዘላቂነት መቀረፍ አለበት

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት የብሔራዊ የፀረ-ሙስና ኮሚቴ ስለ አከናወኗቸው ተግባራት ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች ምላሽ እና ማብራሪያ ሲሰጡ እንደተናገሩት የፀረ-ሙስና ኮሚቴ መቋቋሙን ተከትሎ ጩኸት በርክቷል፥ ይህም አቁሙ የሚል ነው፣ ኮሚቴው ስራውን አጠናክሮ ይቀጥላል፥ ሙስና በዘላቂነት መቀረፍ አለበት ብለዋል።

በሙስና መረጃ የተያዘባቸው ግለሰቦች ከተጠያቂነት ለማምለጥ የሀገሪቱን ወቅታዊ ችግሮች የህዝብን ቁስል በሚነካ መልኩ እያከኩ ይጮሃሉ፥ ችግሩ ውስብስብ እጆች እና የፖለቲካ ሴራ ያለበት በመኾኑ በቀላሉ የሚፈታ አይደለም ሲሉ ተደምጠዋል።

እርዳታን በተመለከተ አደገኛ ልምምድ እየተለመደ ነው፥ በተረጂዎች ስም ሌብነት እየተስፋፋ ነው፤ እርዳታ ችግርን ለመሻገሪያ መሆን አለበት፤ በተለያዩ አካባቢዎች በድርቅ ምክንያት የተከሰቱ ችግሮችን ለመቅረፍ እየተሰራ ነው፡፡ እዳ መቀነስ፣ ምርትን ማሳደግ፣ ሌብነት መቀነስ እና ሰላምን ማረጋገጥ ቀዳሚ ስራዎች ሊሆኑ እንደሚገባ ገልፀዋል፡፡

**መንግስት የፀረ-ሙስና ትግሉን በልዩ ሁኔታ ለመምራት እየተንቀሳቀሰ በመሆኑ ኮሚሽኑ ለውጤታማነቱ አበክሮ ይሰራል - ኮሚሽነር ክቡር ሳሙኤል ኡርቃቶ (ዶ/ር)**

ገጽ 2

**የቀድሞ የቡሌሆራ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዜዳንት የነበሩት ዶ/ር ጫላ ዋታ በሙስና ወንጀል ተጠርጥረው በቁጥጥር ስር ዋሉ**

ገጽ 4

## በ18 ሺህ የትምህርት ማስረጃዎች ላይ በተደረገ የሕጋዊነት ማረጋገጫ 900 የሚሆኑት ሐሰተኛ ሆነው ተገኝተዋል፡- የትምህርት እና ሥልጠና ባለሥልጣን

በ18 ሺህ የትምህርት ማስረጃዎች ላይ የሕጋዊነት ማረጋገጫ ተደርጎ 900 የሚሆኑት በተለያዩ ምክንያቶች ሐሰተኛ ሆነው መገኘታቸውን የትምህርት እና ሥልጠና ባለሥልጣን አስታወቀ።

የማረጋገጥ ሥራ የተከናወነው በዘንድሮው በጀት ዓመት የትምህርት ማስረጃ ሕጋዊነት እና ትክክለኘነት እንዲረጋገጥላቸው ከጠየቁ 18 ሺህ ደንበኞች መሆኑም ታውቋል።

የትምህርት እና ሥልጠና ባለሥልጣን በተቀናጀ ከፍተኛ ትምህርት ፍቃድ አሰጣጥ፣ የፍቃድ እድሳት፣ ክትትል እና ቁጥጥር ዙሪያ በትብብር ለመሥራት ከባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት ባካሄደበት ወቅት የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር አምባሳደር ሽፈራው ሽጉጤ በመድረኩ ላይ ባስተላለፉት መልእክት፣ ሐሰተኛ የትምህርት ማስረጃ ጉዳይ እየተባባሰ መምጣቱን ገልጸዋል።

በዘንድሮው በጀት ዓመት እስካሁን 18 ሺህ ደንበኞች የትምህርት ማስረጃ ሕጋዊነትና ትክክለኘነት እንዲረጋገጥላቸው ጠይቀው ከእነዚህ ውስጥ 900 የሚሆኑት በተለያዩ ምክንያቶች ሐሰተኛ ሆነው መገኘታቸውን ተናግረዋል።

በመሆኑም የትምህርት እና ሥልጠና ጥራትን እና አግባብነትን እንዲሁም ትክክለኛነትን ለማረጋገጥ የጋራ ጥረት የሚጠይቅ መሆኑን ገልጸዋል።

የትምህርት ማስረጃዎቹ ተመሳስለው የተሠሩ፣ እውቅና ከሌለው ተቋም የተሰጡ፣ ባልተፈቀደ የሙያ መስክ የሠለጠኑ፣ የመቁረጫ ነጥብ እና የብቃት ማረጋገጫ ሳይኖራቸው የሠለጠኑ ስለመሆኑም አብራርተዋል።

በአንዳንድ የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ላይ በተደረገው ማጣራት ከባለሥልጣኑ እውቅና ውጭ ካምፓስ በማስፋፋት ፍቃድ ባላገኙበት የትምህርት ዘርፍ ሥልጠና ሲሰጡ መገኘታቸውንም አረጋግጠናል ብለዋል።

ባልተፈቀደላቸው የትምህርት መርሐ-ግብር እና ከተቀመጠላቸው ቁጥር በላይ ተማሪዎችን ተቀብለው ሲያስተምሩ የነበሩም መገኘታቸውን ጠቅሰዋል።







# በመንግሥት ውስጥ የሚገኙ ሌቦች፣ በባለሀብቱ አካባቢ ያሉ ሌቦች፣ በብሔር ዙሪያ ያሉ ሌቦችና በሚዲያው አካባቢ ያሉ ሌቦች ለአንድ ዓላማ አራት ሆነው እየሠሩ ሀገር እያጠፉ ነው - የብልፅግና ፓርቲ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ

የአራት ኃይሎች የጋራ ግንባር ፈጥረው እየፈጸሙት ያሉት ሌብነት የድህነት ወገባችንን እያደቀቀው መሆኑን ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው በአጽንዖት ተመልክቶታል፡፡

በመንግሥት ውስጥ የሚገኙ ሌቦች፣ በባለሀብቱ አካባቢ ያሉ ሌቦች፣ በብሔር ዙሪያ ያሉ ሌቦችና በሚዲያው አካባቢ ያሉ ሌቦች ለአንድ ዓላማ አራት ሆነው እየሠሩ ሀገር እያጠፉ ነው፡፡

በመንግሥት አካባቢ የሚገኙት ሌቦች መዋቅርና ሥልጣናቸውን ይጠቀማሉ፤ በባለሀብቱ አካባቢ ያሉት ሌቦች ደግሞ ገንዘባቸውን ለበለጠ ስርቆት ይጠቀማሉ፤ በብሔር ዙሪያ ያሉት ደግሞ ለሌብነታቸው የብሔር ሽፋን ይሰጡታል፤ በሚዲያ አካባቢ ያሉት ደግሞ የሌቦቹን ገጽታ ይገነባሉ፤ ሌቦቹ ሲያዙም ብሔራቸውን እየጠቀሱ ሕዝብ የተነካ ያስመስላሉ፡፡

ሁሉም ዓይነት ሌቦች ፍትሐዊነትን ያዛባሉ፤ የሕዝብን ደም ይመጣሉ፤ ስርቆታቸው እንዳይደረስበት ግጭትና አመጽ ያስቀሰቅሳሉ፡፡

መንግሥት ሁሉንም ዓይነት ሌቦች ለማጥፋት የጀመረውን ዘመቻ አጠናክሮ ይቀጥላል፡፡ ለዚህም የፓርቲው አመራሮች፣ አባላትና ደጋፊዎች እጃቸውን አስቀድመው ንጹሕ በማድረግ ትግሉን እንዲመሩ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ጥሪ መቅረቡን የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት አጋርቷል፡፡

ሕዝባችንም በሌቦች ላይ የተጀመረው ዘመቻ ግቡን እንዲመታ መረጃ በመስጠት፣ የሌቦች ተባባሪ ባለመሆንና ከሌብነት የጸዳ ትውልድ በማነጽ ኢትዮጵያን እንዲታደግ ጥሪ ቀርቧል፡፡

# መንግስት የፀረ-ሙስና ትግሉን በልዩ ሁኔታ ለመምራት እየተንቀሳቀሰ በመሆኑ ኮሚሽኑ ለውጤታማነቱ አበክሮ ይሰራል - ኮሚሽነር ክቡር ሳሙኤል ኡርቃቶ (ዶ/ር)

ኮሚሽኑ ከ500 በላይ ለሚሆኑ የፌደራል ተቋማት እና ለልማት ድርጅቶች የሥነምግባርና ፀረ-ሙስና መከታተያ ክፍል፣ የውስጥ ኦዲት አገልግሎት፣ የሕግ አገልግሎት እና የተቋማዊ ለውጥ ስራ ኃላፊዎች ቢሾፍቱ ኪሎሌ ሆቴል በሁለት ዙር የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና አካሄደ፡፡








የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናው በዋናነት በስነምግባራዊ አመራር፣ ኦዲትና ስነምግባር፣ የሙስና ወንጀሎችና ድንጋጌዎች እንዲሁም የሙስና መከላከያ ስልቶችና ቅንጅታዊ አሰራር በሚሉ ርዕሰ ጉዳዮች ያተኮረ ነበር፡፡

የኮሚሽኑ ኮሚሽነር ክቡር ሳሙዔል ኡርቃቶ (ዶ/ር) መድረኩ ተገኝተው እንደገለፁት፥ የተቋማት አሰራር ግልፀኝነትና ብቃት ለማሳደግ እነዚህ የስራ ክፍሎች ተናበውና ተባብረው መስራት ይኖርባቸዋል፡፡ ክፍሎቹ ኃላፊነታቸውን ሳይሸራርፉ በቅንጅት ከተንቀሳቀሱ በርካታ የሙስና ስጋቶችን መቀነስ ይቻላል ብለዋል፡፡

የፀረ-ሙስና ትግል የፖለቲካ ቁርጠኝነት የሚጠይቅ መሆኑን የጠቀሱት ኮሚሽነሩ፥ አሁን ባለው ምቹ የፖለቲካ ምህዳር በተግባር መስራት ከተቻለ ሙስናን ከብሄራዊ ስጋት ማውረድ እንደሚቻል ገልፀዋል።

መንግስት የፀረ-ሙስና ትግሉን በልዩ ሁኔታ ለመምራት እየተንቀሳቀሰ በመሆኑ ኮሚሽኑ ለውጤታማነቱ አበክሮ እንደሚሰራ አስገንዝበዋል፡፡

ኮሚሽነሩ በማጠቃለያ ንግግራቸው ካነሷቸው ሀሳቦች መካከል፡- በየተቋማቱ ያሉ ዋልጌ አመራሮችን፣ ህግ ማስከበርና ማክበር ሳይሆን ራሳቸው ህግ የሆኑትን ስርዓት ማስያዝ እንደሚገባ፣ 2.6 ቢሊዮን ዶላር በየአመቱ ከታዳጊ ሀገራት እንደሚሸሽ፣ ሙሰኞች ግጭት እንደሚፈልጉና ሰላም እንደማይወዱ፣ የፀረ-ሙስና ኮሚቴው ስራውን እንደሚቀጥል፣ ሙሰኛ አመራር በተገኘው መረጃ ልክ ተጠያቂ እንደሚሆን፣ የዘረፈውንም ሀብት ተመላሽ እንደሚደረግ እና ባለፉት ወራት ከ2000 በላይ የሙስና ፍሬ ሃሳብ የያዘ ጥቆማ እንደቀረበ፣ ይህን ስራ ሰልጣኞች ማገዝ እንዳለባቸው እንዲሁም በጋራ የተጀመረው የግንዛቤ ስራ ወደ ፎረም አድጎ ቢያንስ በየሩብ አመቱ ግንኙነት እንደሚኖርና እንደሚገመገም እንዲሁም የተሻለ ስልጠና በቀጣይ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል አብራርተዋል፡፡

ምክትል ኮሚሽነር ክቡር ወዶ አጦ በበኩላቸው ሙስና ዜጎች በሰላም እንዲኖሩ የምናልመውን ህልም ጭምር የሚያቀጭጭ ችግር መሆኑን ገልፀው ችግሩን መታገል የሁላችን የጋራ ኃላፊነት ነው ብለዋል። ሙስና ትቂቶች በሚሰርቁበት ጉዳቱ የሚያርፈው በሁላችን ላይ ከመሆኑም በላይ ሀገር የማፍረስ አቅም ያለው በሽታ ነው። ስለዚህ ሁላችንም በጋራ በየዓለንበት የስራ መስክ በመዋጋት እንደ ሀገር የተፅዕኖ ደረጃውን የመቀነስ ኃላፊነት ይኖርብናል ብለዋል።

የሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ስልጠና መሪ ስራ አስፈፃሚ አቶ ዳግም አላምረው የስልጠናው ዋና አላማ በዚህ የስራ መስክና አደረጃጀት ያሉ አባላትን አደራጅቶ ሙስና ለመታገል የሚያስችል አቅም፣ አደረጃጀትና ጉልበት እንዲሁም የመረጃ ትስስር መፍጠር መሆኑን አብራርተዋል። ከዚህ በፊት እንደተለመደው አቅም ፈጥሮ የሚተው ስራ አይደለም፡፡ ሰልጣኞች በየተቋማቱ ሲመለሱ የጋራ እቅድ አውጥተው ተቀናጅተው እንዲሰሩ፣ አመራሩ ድጋፍ እንዲያደርግና እንዲገመግም ለኮሚሽኑ ደግሞ ሪፖርት የሚደረግበት አሰራር ይዘረጋል፡፡ ስርዓቱ ወደመሬት ወርዶ ሲተገበር መንግስት የጀመረውን ብሔራዊ የፀረ-ሙስና ዘመቻ በመደገፍ ረገድ የራሱ ሚና ይኖረዋል ብለዋል፡፡

በስልጠናው አስተያየት የሰጡ ተሳታፊዎች እንደገለጹት፥ በየተቋማቱ ተስፋፍቶ ያለውን ብልሹ አሰራር በትብብር ለመቅረፍ መድረኩ ከፍ ያለ ሚና እንደሚኖረው ተስፋ እንደሚያደርጉ ገልፀዋል፡፡

በቡናና ሻይ ባለስልጣን የተቋማዊ ለውጥ ስራ አስፈጻሚ የሆኑት አቶ ስንታየሁ ወ/ሚካኤል አራቱንም የስራ ክፍሎች በማቀናጀት መሰጠቱ ጥሩ ጅምር መሆኑን በማንሳት የትብብር እና የቅንጅት ስራ ለፀረ-ሙስና ትግል ብቻ ሳይሆን ለሌሎች ተግባራትም አስፈላጊ መሆኑን አስተያታቸውን ሰጥተዋል፡፡

**የመንግስት አመራሮች የግልጽነትና የተጠያቂነት አሰራር ስርዓት በማጎልበት ተቋማችንን ከሙስና እና ብልሹ አሰራር ጽዱ ማድረግ ይችላሉ፤ ይጠበቅባቸዋል**

በተለይ የፀረ-ሙስና ትግል ደግሞ የትብብር ስራን ይበልጥ የሚፈልግ በመሆኑ ኮሚሽኑ በቀጣይም እንደዚህ አይነት መድረክ በመፍጠር ሚናውን እንዲወጣ አስገንዝበዋል፡፡

የፌደራል ማረሚያ ቤት ኮሚሽን የሥነምግባር እና የፀረ ሙስና ስራ አስፈጻሚ ወ/ሮ የምስራች አካሉ በበኩላቸው የሙስና እና የስነምግባር ስልጠናዎች በርካታ ጊዜ የሚሰጡ ቢሆንም ይህ መድረክ ግን ለተለያዩ የስራ ክፍል ኃላፊዎች የየራሳቸውን ሚና በሚያሳይ መልኩ እየተሰጠ በመሆኑ ለየት እንደሚያደርገው ገልጸዋል፡፡

የፀረ-ሙስና ትግል የአንድ ክፍል ስራ አለመሆኑን በመገንዘብ በቀጣይ በጋራ እንዲሰራ ግንዛቤ እንደሚፈጥር ጨምረው ተናግረዋል፡፡ ኮሚሽኑም በቀጣይ ለውጤታማነቱ አበክሮ እንዲሰራ ጠይቀዋል፡፡

ሌላው አስተያየታቸውን የሰጡት በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን የህግ አገልግሎት ስራ እፈጻሚ የሆኑት አቶ ብዛየነ ገ/እግዚያብሔር ሲሆኑ፥ በፀረ-ሙስና ስራዎች በርካታ አመታትን እንደሰሩ በመጥቀስ ከስልጠናው ባሻገር የህግ ማሻሻያ ስራዎች ላይ መስራት ቢቻል ኮሚሽኑ የተሻለ ቁመና እንደሚኖረው ጠቁመዋል፡፡

የሥነ-ምግባር ግንባታ እና የሙስና መከላከል ስራ ቀዳሚ ተግባር ቢሆንም ሙስና የሚሰሩትን አስተማሪ ቅጣት እንዲያገኙ የማድረግ ኃላፊነት ጭምር ቢኖረው የተሟላ አደረጃጀት ይኖረዋል የሚል እምነት እንዳላቸው ገልፀዋል፡፡

ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

# ፀረ-ሙስና

## በፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሚዘጋጅ ወርሃዊ ጋዜጣ

ስልክ 011552-77-79
ፖ.ሳ.ቁ 34799
ኢ-ሜይል FeaccEthiopia2013@et
ድረ-ገጽ www.feacc.gov.et
ፌስቡክ www.facebook.com/feaccOfficial
ቴሌግራም t.me/feacc
ትዊተር www.twitter.com/EthiopiaFeacc
ዩቲዩብ Federal Ethics & Anti-Corruption Commission

**ለሀብት ማሳወቅና ምዝገባ ስራዎች**
**www.feaccdars.gov.et**

## ለፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሙስና ወንጀል ጥቆማ መስጫ አድራሻዎች

ስልክ 011552-77-92/ 011553-38-52
ሞባይል 0935947533
ፖ.ሳ.ቁ 34799
ድረ-ገጽ www.feacc.gov.et
ኢ-ሜይል CorruptionReportEthiopia@feacc.gov.et
ቴሌግራም t.me/CorruptionPointing
ዋትስአፕ wa.me/qr/5IGXTSIYUMPBF1

# ርዕሰ -አንቀፅ

## ሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃ ንቅናቄ ለፀረ-ሙስና ትግሉ አይነተኛ ሚና አለው

ኮሚሽኑ ዘርፍ ተኮር ጥናት በማድረግ ሙስናን የመከላከል ተግባር ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ መፍትሄ ለመስጠት ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ ዘርፍ ተኮር ጥናት ከተካሄደባቸው ዘርፎች መካከል የትምህርት ዘርፍ ይገኝበታል፡፡ በዚህ ዘርፍ የተካሄደው ጥናት እንደሚያሳየው ቢከሰቱ ከፍተኛ ጉዳት የሚያስከትሉ የሙስና አይነቶች መካከል ሀሰተኛ ሰነድ በዋነኛነት ይጠቀሳል፡፡

ሀሰተኛ የትምህርትም ሆነ ሌሎች ሰነዶችን መጠቀም ወይም መገልገል እየተለመደ የመጣ የወንጀል ድርጊት መሆኑን መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ በአብዛኛው ሀሰተኛ ሰነዶች የሚፈጠሩበትና ለአገልግሎት የሚውሉበት ምክንያትም ህገ ወጥ ኢኮኖሚያዊ፤ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ጥቅም ለማግኘት ያለመ እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡ ከሀሰተኛ ሰነዶች እንዲሁም ህገ ወጥ ደረሰኞች ጋር በተያያዘ የሚፈጸሙ ወንጀሎች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመሩ መምጣታቸውን ለማረጋገጥ ሰፊ ጥናት በማድረግ የችግሩ ስፋት ማወቅ ተገቢ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በየጊዜው ለምርመራ ከሚቀርቡ ሀሰተኛ ሰነዶች ለመረዳት እንደሚቻለው ችግሩ አሳሳቢ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡

ሀሰተኛ ሰነድ አንድ አይነት መልዕክት ማስተላለፍ የሚችል በፊደል፣ በቁጥር፣ ወይም በታወቁ ምልክቶች መልክ በማንኛውም ጽሑፍ በሚቀበል ቁስ ህጋዊ የሆነውን ነገር ተመሳስሎ ሲሰራ/ሲፈጠር ወይም ትክክለኛ መልዕክት ማስተላለፍ የሚችሉ መግለጫዎቹ ሲቀየሩ ሀሰተኛ ሰነድ ይባላል፡፡ ሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃ ደግሞ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ የወንጀል ሕግ ሀሰተኛ ሰነዶችን መፍጠር፤ ወደ ሀሰት መለወጥና ማጥፋት እንዲሁም በምስክር ወረቀቶች ላይ የሚደረግ አሰራር ነው፡፡ ጉዳዩን ለመቅረፍ ከዚህ በፊት በኮሚሽኑ በተካሄደ ዘመቻ በጣም በርካታ ሀሰተኛ ሰነዶችን መጋለጥ ተችሏል፡፡ አሁንም በተሻለ መንገድ ቢመራ ጥሩ ውጤት ሊያመጣ ሲይችላል፡፡ ሀሰተኛ የሰነድ ማስረጃን በዚህ ወቅት በንቅናቄ መልክ ለመቀነስ ብሎም ለማስወገድ ያሉ መልካም አጋጣሚዎች፡-

የመንግስት ቅድሚያ ትኩረት መሆኑ፡- በተያዘው የበጀት አመት መንግስት ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ የሚሰራው ሙስናን መታገል መሆኑን ጠቅላይ ሚንስትሩ በተደጋጋሚ በመግለጻቸው ሀሰተኛ ሰነድን እንደ አንድ አጀንዳ በማድረግ መሰረታዊ ለውጥና የህዝብ ንቅናቄ በመፍጠር በርካታ ሀሰተኛ ሰነዶችን የማጋለጥ ተግባር ቢሰራ እንደ መልካም አጋጣሚ ይወሰዳል፡፡


ማህበረሰቡ ዘንድ የሚታየው አመለካከት፡- ማህበረሰቡ ለውጥ ከተጀመረ በኋላ በሁሉም ዘርፍ በተለይም ህዝቡን በሚያማርርባቸው (በስራ ማጣት፣ ያለተገባ ሰው በማይመለከተው ቦታ መመደብ፣ ተገቢ የስራ ማስረጃዎች ሳያሟሉ መቀጥር፣ ሀሰተኛ መንጃ ፍቃድ እና ሌሎችንም ሰነዶች መጠቀም) ቦታዎች ለውጥ ይጠብቃል፡፡ ያንን ለውጥ ለማምጣትና በጥናቱ የተጠቀሰውን የሀሰተኛ ትምህርት ማስረጃ የማጋለጥ ስራ ቢሰራ ለማህበረሰቡ መጠነኛ እፎይታን ይፈጥራል፡፡

የመንግስት ተቋማት መዋቅራዊ ለውጥ፡- ከመንግስት ምስረታ በኋላ በርካታ የመንግስት ተቋማት መዋቅራዊ ለውጥ እያደረጉ እንደሆነ የሚታወቅ ሲሆን፣ ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚስተዋሉ የሀሰተኛ ሰነዶችና ትምህርት ማስረጃዎችን የመጠቀም አዝማሚያዎች ስላሉ ጉዳዩን መቆጣጠርና ማጋለጥ ለመንግስትም ሆነ ለኮሚሽኑ መልካም አጋጣሚ ሲሆን የኮሚሽኑን የማድረግ አቅም ለማጠናከር ያግዛል፡፡ በመሆኑም የተጀመረው ሀሰተኛ ሰነዶችን የማጥራት ስራ በባለድርሻ አካላት ጠንካራ ትብብር ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል፡፡

# የቀድሞ የቡሌሆራ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዜዳንት የነበሩት ዶ/ር ጫላ ዋታ በሙስና ወንጀል ተጠርጥረው በቁጥጥር ስር ዋሉ







ዶ/ር ጫላ የመንግስት ግዥ ህግ ከሚፈቅደው አሰራር ውጭ በመሄድ በመንግስት ሀብት ላይ ከፍተኛ ጉዳት አድረስዋል በሚል የምክር ቤት አባልነታቸው ከተነሳ በኋላ በቁጥጥር ስር እንዲውሉ ተደርጓል፡፡ ግለሰቡ “ቢኤችዩ ኮንሰልቲንግ ኢንጂነሪንግ ጄነራል ሌቭል 1 ፒኤልሲ” የተባለ አማካሪ ድርጅት በማቋቋም በስማቸው ንግድ ፍቃድ በማውጣት ከቡሌሆራ ዩኒቨርሲቲ ጋር የተለያዩ የግንባታ ስራዎችን የማማከር አገልግሎት ለመስጠት በቀጥታ ግዥ በመፈፀም መዋዋሉን፣ ለአማካሪ ድርጅቱና ለአማካሪ ድርጅቱ ላፀደቃቸው ተቋራጮች ክፍያ በመፈፀም በመንግስት ላይ ከፍተኛ ጉዳት እንዲደርስ አድርገዋል በሚል ጥቆማ ደርሶ ዝርዝር ምርመራ ተደርጓል።

የምክር ቤት አባላነታቸው በተነሳበት ወቅት ዝርዝር ምርመራዎች እንደሚያሳዩት ግለሰቡ 195 ሚሊዮን 52 ሺህ 812 ብር ከ81 ሳንቲም የሚያወጡ የተገለያዩ የግንባታ ስራዎች ለ9 ተቋራጮች ከመንግስት የግዥ አዋጆች እና አፈፃፀም መመሪያ ውጭ በቀጥታ እንዲፈፀም አድርገዋል።

በተጨማሪም ዩኒቨርሲቲው ለመሰረተ ልማት ግንባታ የተፈቀደለትን የካፒታል በጀት አላግባብ በመጠቀም የግዥ ህግ እና ደንብ ባልተከተለ መልኩ ዋጋቸው 116 ሚሊዮን ብር የሆኑ 14 ተሽከርካሪዎች እና ማሽነሪዎች በግል ተቋራጭ ድርጅት ስም ግዥ ተፈፅሟል። ከዚህ ጋር በተያያዘ ተሽከርካሪዎቹ እና ማሽነሪዎቹ በዩኒቨርሲቲው ገንዘብ የተገዙ ቢሆንም በግል ተቋራጮች ድርጅቶች ስም እንዲሆኑ ተደርጓል።

ተሽከርካሪዎቹ እና ማሽነሪዎቹ የተገዙበት ዋጋ እጅግ የተጋነነ ሲሆን ለምሳሌ፡- አንድ ደብል ጋቢና ፒካፕ ለተሽከርካሪ ተቋራጭ ድርጅቱ ከአስመጪ በብር 3 ሚሊዮን 300 ሺህ ግዥ የተፈፀመ ቢሆንም ዩኒቨርሲቲው በብር 6 ሚሊዮን 173 ሺህ 396 ብር ከ83 ሳንቲም እንደተገዛ ተቆጥሮ ክፍያ በመፈፀም ብር 2 ሚሊዮን 873 ሺህ 396 ብር እላፊ ተከፍሏል።

አንድ ሌላ ተሽከርካሪ ግዥ የተፈፀመው በብር 6.1 ሚሊዮን ቢሆንም ዩኒቨርሲቲው በብር 6 ሚሊዮን 415 ሺህ 687 ብር ከ05 ሳንቲም በመግዛት ክፍያ የተፈፀመ በመሆኑ 315 ሺህ 687 ብር ከ05 ሳንቲም እላፊ እንዲከፈል ተደርጓል።

አጠቃላይ የ14ቱ ተሽከርካሪዎች እና ማሽነሪዎች ባለቤት የዩኒቨርሲቲው ሳይሆን የስራ ተቋራጭ ድርጅቶቹ እንዲሆኑ በማድረግ የተሰጣቸውን የመንግስት ኃላፊነትን ወደ ጎን በመተው ለራሳቸው የማይገባ ጥቅም በማግኘት እንዲሁም አማካሪ ድርጅት በሌለበት የተቋሙ የግንባታ ፅህፈት ቤት በፀደቁ የክፍያ የምስክር ወረቀት 11 ሚሊዮን 532 ሺህ 83 ብር ከ53 ሳንቲም ለተቋራጮች ክፍያ እንዲፈፀም በማድረግ የመንግሥት ሃብት እና ንብረት እንዲባክን አድርገዋል።

በዶ/ር ጫላ ዋታ እና ቢኤችዩ ኮንሰልቲንግ ኢንጂነሪንግ ጄነራል ሌቭል 1 ፒኤልሲ በተባለው ድርጅት ላይ በተካሄደው የሃብት ምርመራ ስራ በተገኘው ውጤት ድርጅቱን የሚያንቀሳቅሱት ስራ አስኪያጅ እና የቦርድ ዳይሬክተር ዶ/ር ጫላ ዋታ መሆናቸው በዚህም ድርጅቱ ከቡሌሆራ ዩኒቨርሲቲ ጋር በገባው ውል መሰረት በድምሩ 23 ሚሊዮን 135 ሺህ 433 ብር ከ27 ሳንቲም ያለአግባብ ከቡሌሆራ ዩኒቨርሲቲ የባንክ ሂሳብ ላይ ተቀንሶ ወደ ድርጅቱ ሂሳብ ቁጥር ገቢ መደረጉና ከዚህ በመቀጠል ከድርጅቱ ቢኤችዩ ኃ/የተ/የግል ማህበር የባንክ ሂሳን ተቀንሶ በ6 የተለያዩ ጊዜያት በድምሩ 2 ሚሊዮን 116 ሺህ 16 ብር ከ65 ሳንቲም ወደ ዶ/ር ጫላ ዋታ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በተከፈተ የሂሳብ አካውንት ገቢ ተደርጓል።

በዶ/ር ጫላ ዋታ ባለቤት ስም ወ/ሮ ፀሃይ ኃይሉ ተፈራ ስም 72 ካሬ ላይ ያረፈ በብር 10 ሚሊዮን የተገዛ ባለ 3 ወለል ህንፃ የተገኘ መሆኑና ህንፃው የተገዛበት ገንዘብ በተመለከተ የተደረገው የፋይናንስ ምርመራ ክፍያው የተፈፀመው “ቢዳሩ ኮንስትራክሽን” ከተባለ ድርጅት ብር 4 ሚሊዮን እንዲሁም አቶ ተስፋሁን ሌንጂቦ ሌካ ብር 3 ሚሊዮን 500 ሺህ፥ በተጨማሪ በዚህ ተመሳሳይ ቀን ቦኩይ ኢታንሳ የተባሉ ብር 2 ሚሊዮን 500 ሺህ በዶ/ር ጫላ ዋታ ባለቤት ወ/ሮ ፃሃይ ኃይሉ ተፈራ ስም ወደ ተከፈተ የሂሳብ ቁጥር ገቢ ተደርጎ ይኸው ገንዘብ በቀጥታ ለህንፃው ግዥ መዋሉ ታውቋል።

ገንዘቡ ለባለቤታቸው ለወ/ሮ ፀሃይ ኃይሉ ገቢ አድራጊዎች ማንነት ለማጣራት በተደረገው ምርመራ መሰረት በ “ቢዳሩ ኮንስትራክሽን” በቡሌሆራ ዩኒቨርሲቲ ገንዘብ የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 3 አአ 05069 የሆነ በብር 7 ሚሊዮን 785 ሺህ 157 ከ30 ሳንቲም የተገዛለት መሆኑና ተስፋሁን ሌንጂቦ የተባለው ደግሞ ቡሌሆራ ዩኒቨርሲቲ ለሚያሰራቸው ግንባታ መሰረተ ልማት እና ኢንፍራስትራክቸር ዝርጋታ ስራ በቀጥታ በደብዳቤ ትዕዛዝ 55 ሚሊዮን 133 ሺህ 893 ብር ስራ የተሠጠው ነው።

በዶክተር ጫላ ዋታ ስማቸው የተመዘገበ በን/ስ/ላፍቶ ክ/ከተማ አንድ ሙሉ ክፍያው የተፈፀመ ኮንዶሚኒየም ቤት በልጃቸው ስም 200 ሺህ ብር በራሳቸው ስም የተገዛ የ1 ሚሊዮን ብር ሼር የተገኘ መሆኑ ተረጋግጧል።

የቀድሞ የቡሌሆራ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ጫላ ዋታ ( ዶ/ር) ላይ በተከፈተ የጊዜ ቀጠሮ መዝገብ ፍርድ ቤት ቀርበዋል፡፡

ተጠርጣሪው በዩኒቨርሲቲው ኃላፊ በነበሩበት ወቅት የግዢ መመሪያን ባልተከተለ መንገድ የንብረት ግዢ ማከናወን፣ ህግን ያልተከተለ የስራ ተቋራጭ ውል መፈጸም እና ወደ ስራ ማስገባት እንዲሁም ያልተገባ ጥቅም በማግኘት የሙስና ወንጀል ተጠርጥረው ምርመራ መጀመሩን ፖሊስ ለችሎቱ አስረድቷል።

በዚህም መነሻ የሰነድ ማስረጃዎችን መሰብሰቡን ያብረራው መርማሪ ፖሊስ÷ ቀሪ የሰነድና የሰው ምስክር ቃል ለመቀበልና ተጨማሪ የ14 ቀን የምርመራ ጊዜ እንዲሰጠው ጠይቋል።

ተጠርጣሪው በበኩላቸው÷ ምንም ወንጀል አልፈጸምኩም ሲሉ በመከራከር የዋስትና መብታቸው እንዲከበር ጠይቀዋል።

መርማሪ ፖሊስ በዋስ ቢወጡ ማስረጃ ሊያሸሹብኝ፤ ምስክር ሊያባብሉብኝ ይችላሉ በማለት ስጋቱን ገልጾ የዋስትና ጥያቄያቸውን በመቃወም መከራከሩን ፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት አመላክቷል።

የምርመራ መዝገቡን የተመለከተው ጊዜ ቀጠሮ ችሎቱ የተጠርጣሪውን የዋስትና ጥያቄ ለጊዜው ውድቅ በማድረግ ተጨማሪ ምርመራ ማስፈለጉን በማመን ፖሊስ የጠየቀውን የ14 ቀን ተጨማሪ የምርመራ ጊዜ ፈቅዷል።

# የእምነት ተቋማት ሌብነትን ፊት ለፊት በመታገል ሚናቸውን ሊወጡ ይገባል



በሀገሪቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተስፋፋ የመጣውን የመልካም አስተዳደር ችግርና ሌብነት ፊት ለፊት በመታገልና ለሕዝቡ አርአያ ሆኖ በመገኘት ረገድ ሁሉም የእምነት ተቋማት ኃላፊነታቸውን ሊወጡ እንደሚገባ የሃይማኖት መምህሩ ኡስታዝ አቡበከር አሕመድ አሳሰቡ፡፡

ሕዝበ ሙስሊሙ በተያዘው የረመዳን ፆም የተቸገሩትን በመርዳትና የሃገሪቱን ሰላምና አንድነት በማስጠበቅ ረገድ የበኩሉን ሚና ሊወጣ እንደሚገባም አስገንዝበዋል፡፡

እንደሀገር የመልካም አስተዳደርና የሌብነት ተግባር እየተስፋፋ መምጣቱ የሀገሪቱን ችግር በመሆን ለማኅበረሰባዊ ሥነ-ምግባር መላሸቅ በተለይም ቤተ እምነቶች በፈጣሪ የተሰጣቸውን ኃላፊነት በሚገባ መወጣት አለመቻላቸው አንዱ ምክንያት መሆኑን ገልፀው፥ በተለያየ ቦታ ላይ በኃላፊነት ያስቀመጥናቸው አንዳንድ ሰዎች ሃገርን እየዘረፉና በማጭበርበር እንዲሁም በማምታታት ብዙ ጥፋት ሲያጠፉ እንመለከታለን››::

አንዳንድ የእምነት አባቶች አጥፊዎችን ገስፆ ከመመለስ ይልቅ የተግባሩ ተሳታፊ ሆነው መገኘታቸው ሀገሪቱን ለችግር የዳረጋት መሆኑንም መጥቀሳቸውን ኢትዮጵያ ፕረስ ድርጅት ዘግቧል።

እንደማኅበረሰብ የጠፋውን የሞራልና የሥነ-ምግባር ከፍታ መልሶ ለመገንባት ቤተ-እምነቶች ያላባቸውን ኃላፊነት በአግባቡ ሊወጡ እንደሚገባ የተናገሩት ኡስታዝ አቡበከር፥ "ሕዝብና ሃገርን እያጠፋ ያለውን የሌብነት ተግባር የሚያስቆም፤ ሕግና ሥርዓት ለማስከበር በሥነ-ምግባሩ የታነፀ ትውልድና ሀገር መፍጠር የሚያስችል ሥራ መሥራት ይጠበቅባቸዋል" ብለዋል።

ትክክለኛውን ሃይማኖታዊ አስተምህሮና መርሆ ለሕዝቡ በማድረስ፤ ራሳቸውን ከሌብነትና ከመልካም አስተዳደር ችግር በማጥራት ሕግና መርሕን ጥሰው የተገኙ አካላትንም ፊት ለፊት በማጋለጥ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ጥሪ አቅርበዋል።

በተያዘው የረመዳን ፆም ሕዝበ-ሙስሊሙ የአላህ ዋነኛ መርሆ የሆኑትን በተለይም የተቸገሩ፣ የተራቡና ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለው ለአደጋ የተጋለጡትን ዜጎች ዘር ቀለም ሳይለይ ሊደግፍ እንደሚገባ አስገንዝበዋል።

ከዚሁ ጎን ለጎንም የእስልምና ዋነኛ መርሕ የሆነውን ሰላምና የሃገር አንድነትን በማስጠበቅ ረገድ ምዕመኑ የበኩሉን ድርሻ መወጣት እንዳለበት ተናግረዋል።

አክለውም "ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የሃይማኖትና የቋንቋ ልዩነት ውበት ብቻ ሳይሆን ለሃገራችን እድገት ትልቅ አቅም በመሆኑ ልንጠቀምበት ይገባል" ብለው፤ ልዩነቶች አንዱ የሌላው ደካማ ጎን መሙያ እንጂ ስጋት ወይም መከራ ሊሆኑ እንደማይገባ አሳስበዋል፡፡

# የመንግስት አገልግሎት አሰጣጥን ለማሻሻል እየተሰራ ነው - የኦሮሚያ ክልል ምክትል ፕሬዚደንት አወሉ አብዲ

በኦሮሚያ ክልል የመንግስት አገልግሎት አሰጣጥን ለማሻሻል በትኩረት እየተሰራ መሆኑን የክልሉ ምክትል ፕሬዚደንት አወሉ አብዲ ገለጹ።

በክልሉ በመንግስት አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሚታዩ ችግሮችን ለመቀነስና በአገልግሎት ማሻሻል ላይ በተሰሩ ስራዎች 40ሺህ በሚጠጉ አመራሮችና ሙያተኞች ላይ የተለያየ እርምጃ መወሰዱንም አስታውቀዋል።

የክልሉ ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ አወሉ አብዲ ከኢዜአ ጋር በነበራቸው ቆይታ እንደገለፁት የክልሉ መንግሥት የተገልጋዩን ህብረተሰብ የመልካም አስተዳደር ችግር ለመፍታትና ብልሹ አሰራሮችን ለማስወገድ በትኩረት እየሰራ ነው።

በተለይም ባለፉት ሰባት ወራት የመልካም አስተዳደር ችግር የሚስተዋልባቸውን ተቋማት ለመለየት በክልሉ ፕሬዚደንት የቅርብ ክትትል የሚደረግበት ልዩ ግብረ-ሃይል በማደራጀት ሲሰራ መቆየቱን ተናግረዋል።

ከዚህም በተጨማሪ በምክትል ፕሬዚደንት የሚመሩ ልዩ ኮሚቴ ተቋቁሞ ወደ ስራ መገባቱን አቶ አወሉ አብዲ ገልጸዋል።

ኮሚቴውም የመጀመሪያ ስራው ችግሮችን መለየት ላይ ትኩረት አድርጎ በመሰራቱ በክልሉ መስሪያ ቤቶች ላይ የሚስተዋሉ ክፍተቶችን መለየት ተችሏል ብለዋል።



በዚህም በሁሉም መስሪያ ቤቶች ላይ የአገልግሎት አሰጣጥ ችግሮች መኖራቸውን በማረጋገጥ ወደ መፍትሄ ዕቅድ ዝግጅት መገባቱን ተናግረዋል።

የመንግስት ስራ ሰዓት ካለማክበር ጀምሮ ብዙ ችግሮች መኖራቸውን የጠቀሱት አቶ አወሉ "አብዛኛው ሰራተኛ አራት ሰዓት ቢሮ ገብቶ ዘጠኝ ሰዓት እንደሚወጣ በተለያየ ጊዜ ከተገልጋዮች ጋር በተደረጉ ውይይቶች ማረጋገጥ ተችሏል" ብለዋል።

በዚህም አገልግሎት ፈላጊው ህዝብ ከመጉላላት ባለፈ 'እጅ መንሻ' ጭምር እየተጠየቀ መሆኑን መረዳት እንደተቻለ ተናግረዋል።

እንደ ምክትል ፕሬዚዳንቱ ገለፃ አንዳንድ አመራሮችም ስብሰባዎችን ጨምሮ የኮሚቴና ሌሎች ጉዳዮችን ሽፋን በማድረግ የመልካም አስተዳደር ችግር እየፈጠሩ መሆናቸው መረጋገጡን ጠቅሰዋል።

ችግሮቹ ከተለዩ በኋላም በየመስሪያ ቤቱ መፍትሄ ማምጣት የሚያስችሉ ሪፎርሞች እንዲካሄድ በመደረጉ የተወሰኑ ለውጦች ታይተዋል ብለዋል።

በተለዩት ችግሮች መነሻ በማድረግ ችግሮቹን ለመቀነስና የአገልግሎት አሰጣጡን ለማሻሻል 40ሺህ በሚጠጉ አመራሮችና ሙያተኞች ላይ የተለያየ እርምጃ ተወስዷል ብለዋል።

እርምጃ የተወሰደባቸው አመራሮችና ሰራተኞች በሙስናና 'እጅ መንሻ' በመጠየቅ፣ ሌብነትና ብልሹ አሰራር ውስጥ በመሳተፍ መረጃ የተገኘባቸው መሆኑን ተናግረዋል።

የተወሰደው እርምጃም ከቃል ማስጠንቀቂያ ጀምሮ ከቦታ ማንሳት፣ ከደረጃና ከደመወዝ ዝቅ ማድረግ፣ ከስራ ማሰናበትና በህግ ተጠያቂ ማድረግ ጭምር የሚያካትት መሆኑንም አስረድተዋል።

በንግድ፣ መሬት፣ ማዘጋጃ ቤት፣ ፍርድ ቤቶችን ጨምሮ የህዝቡ የዕለት ተዕለት አገልግሎት የሚበዛባቸው ተቋማት ላይ አገልግሎቱን ወደ 'ዲጂታል' የማስገባት ስራ እየተሰራ መሆኑን ገልጸዋል።

በተለይም ከመዝገብ ቤት ጀምሮ ያለውን የአገልግሎት አሰጣጥ ለመለወጥና ከሰው ንክኪ ነፃ ለማድረግ የቴክኖሎጂና ዲጂታላይዜሽን አገልግሎት መጀመራቸውን አክለዋል።

በተጨማሪም እያንዳንዱ አመራር በሳምንት ሶስት ቀን ቀኑን ሙሉ ቢሮ ሆኖ ህዝቡን እንዲያገለግል የክልሉ መንግስት ወስኖ ወደ ተግባር መግባቱን ተናግረዋል።

ከዚህም ባለፈ በክልል ደረጃ በምክትል ፕሬዝዳንቱ የሚመራ የተለያየ ኮሚቴ ተደራጅቶ ክትትልና ቁጥጥር በማድረጉ በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ ከወረዳ ጀምሮ በከተሞችና በዞኖች መሻሻሎች መኖራቸውን አመልክተዋል።

ይሁንና ችግሮቹን በመሰረታዊነት ለመቅረፍ ሪፎርምና ማሻገር ላይ በቀጣይ ስራ የሚፈልጉ ጉዳዮች መሆናቸውን አቶ አወሉ አብዲ ጠቁሟል፡፡

# በረቀቀና በተወሳሰበ መንገድ እየተስፋፋ ያለውን ሙስና እና ብልሹ አሰራር ለመግታት በትብብር መስራት ወሳኝ ነው - በፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን የወንጀል ምርመራ ቢሮ ኃለፊ ም/ኮሚሽነር ዘላለም መንግስቴ



የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ከየተባበሩት መንግስታት ድርጅት የወንጀል እና የዕፅ ቁጥጥር ቢሮ (UNODC) ጋር "በንግድ ስራ ሀቀኝነትን ለማሳደግ የግሉን ዘርፍ አቅም ማጎልበት" በሚል ርዕስ ባዘጋጁት መድረክ የክብር እንገዳ ሆነው የተገኙት በፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን የወንጀል ምርመራ ቢሮ ኃለፊ ም/ኮሚሽነር ዘላለም መንግስቴ እንደገለፁት በተራቀቀና በተወሳሰበ መንገድ እየተስፋፋ ያለውን ሙስና እና ብልሹ አሰራር ለመግታት በትብብር መስራት ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡

በችግሩ ውስብስበነት ምክንያት ዜጎች የሚገባቸውን አገልግሎት ያለክፍያ ለማግኘት የማይችሉበት ሁኔታ ላይ መድረሳቸውን የገለፁት ም/ኮሚሽነሩ መንግስት፣ የግሉ ዘርፍ፣ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች እንዲሁም መገናኛ ብዙኃን በትብብር እና በቅንጅት በመስራት ችግሩን ማጥፋት ባይቻልም መቀነስ መቻል እንደሚኖርባቸው አስገንዝበዋል፡፡



በመድረኩ የተገኙት በኢትዮጵያ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ሪዝደንት ማስተባበሪያ (UN-RCO) ቢሮ ኃላፊ ሃና ኤልሳቤት በበኩላቸው ኢትዮጵያ በምታካሂደው የልማት ጉዞ እና ሙስናን የመታገል ተግባር ድርጅቱ ሁሉን አቀፍ ድጋፉን አጠናክሮ እንደሚቀጥል ተናግረዋል።

በመድረኩ በጉደዩ ዙሪያ የፓናል ውይይት የተካሄደ ሲሆን፥ በተለይ በፀረ-ሙስና ትግሉ የግሉን ዘርፍ ሚና በመጥቀስ ከመንግስት እና ከሌሎች ባለ ድርሻ አካላት ጋር የትብብር ደረጃውን ከፍ ሊያደርግ የሚችሉ ሃሳቦች በስፋት ተንፀባርቀዋል፡፡ በቀረቡ ሃሰቦች ላይ ከመድረኩ አስተያየትና ጥያቄዎች ተነስተው ምላሽ ተሰጥቶባቸዋል፡፡



# ምክር ቤቱ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ዳኛ የነበሩትን አቶ ፋንታሁን ደለለውን ከስራ አሰናበተ

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በ2ኛ ዓመት የስራ ዘመን 2ኛ ዓመት 12ኛ መደበኛ ስብሰባው የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ዳኛ የነበሩትን አቶ ፋንታሁን ደለለው ሽፈራውን ከስራ አሰናብቷል።

የስራ ስንብት ውሳኔ ሃሳቡን ያቀረቡት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሕግ እና ፍትሕ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ወይዘሮ እፀገነት መንግስቱ፤ አቶ ፋንታሁን የዳኞች የስነ-ምግባርና የዲሲፕሊን ክስ ስነ-ስርዓት ደንብ በመተላለፍና የሐቀኝነት ተነጻጻሪ ግዴታ በመተላለፍ ከአመልካች ብር 100ሺህ መደለያ መቀበላቸው በማስረጃ ተረጋግጧል ብለዋል።

ምክር ቤቱም የቀረበለትን የውሳኔ ሃሳብ ሪፖርት ካዳመጠ በኋላ የአቶ ፋንታሁን ደለለው ሽፈራውን የስራ ስንብት የውሳኔ ሃሳብ ቁጥር 13/2015 አድርጎ በሙሉ ድምጽ አጽድቋል፡፡








# "ሙስናን በመታገል ሕጋዊነትን ማስፈን እና ሕገወጥነትን መቆጣጠር ይገባል" በአማራ ክልል የፀረ-ሙስና አስተበባሪ ኮሚቴ

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ክልላዊ የፀረ-ሙስና አስተባባሪ ኮሚቴ ክልላዊ ጥምረት ለላቀ የሙስና ትግል በሚል መሪ ሀሳብ ምክክር እያደረገ ነው።

በአማራ ክልል የክልላዊ የፀረ-ሙስና አስተባባሪ ኮሚቴ ሰብሰቢ ቢያዝን እንኳሆነ በምክክሩ ላይ እንደተናገሩት ክልሉ በለውጥ ሂደት ላይ ነው። በዚህ የለውጥ ሂደት ውስጥ ግን በርካታ ለውጡን የሚያደናቅፉ ችግሮች ተከስተዋል ብለዋል።

ከነዚህ ችግሮች አንዱ ከጦርነት ያልተናነሰው ሙስና ስለመኾኑም ነው የገለጹት። ሙስና ያሰብነውን እንዳናሳካ፣ ካለምነው እንዳንደርስና አንድነታችን እንዳይጠናከር የሚያደርግ ከጦርነት ያልተናነሰ ፈተና ነው ብለዋል።

ሙስና የሰላም ትግሉን አደጋ ውስጥ የሚከት የመልካም አሥተዳደር ችግር እየፈጠረ በመንግሥት እና በሕዝቡ መካከል ሰላም እንዳይኖር የሚያደርግ እንቅፋት በመኾኑ በጋራ መመከት እንደሚያስፈልግም አስረድተዋል።

የፍትሕ ተቋማት የፀረ-ሙስና ትግሉን እንዴት ይደግፉት፣ እንዴት የሕዝቡን በሰላም የመኖር ጥያቄ ምላሽ ይስጡ የሚል ሀሳብ በምክክሩ ላይ ትኩረት የሚደረግበት ሃሳብ መኾኑንም አንስተዋል።

ሰብሰቢው ሙስናን በመታገል ሕጋዊነትን ማስፈን፣ ሕገወጥነትን መቆጣጠርና የሕግ የበላይነትን ማስፈን ከሁሉም የሚጠበቅ ጉዳይ ነው ብለዋል።

በክልል ደረጃ የተቋቋመው ኮሚቴ ከየዞኑ እና ከሌሎች ኮሚቴዎች ጋር በመቀናጀት ሥራዎችን በአግባቡ ሊሠራ ይገባል ብለዋል።

በተያያዘ መረጃ የአማራ ክልል ፀረ-ሙስና ኮሚቴ በሦስት ወራት ከ62 ሺህ ካሬ ሜትር በላይ መሬት እና 27 ሚሊየን ብር ማገድ መቻሉን የኮሚቴው ሰብሳቢ አቶ ቢያዝን እንኳኾነ አስታውቀዋል።

በአማራ ክልል ፀረ-ሙስና ኮሚቴ ከተቋቋመ 3ወር አስቆጥሯል። አቶ ቢያዝን ሥራውን በአግባቡ ለመሥራት የተዋረድ አደረጃጀቶች ተዘርግተዋል ብለዋል። ይህም ውጤት እያስመዘገበ ነው ብለዋል።

አቶ ቢያዝን ሥራውን ለመጀመር እቅድ ተዘጋጅቷል፤ መመሪያዎች ወጥተዋል፣ በወጡ መመሪያዎች እና በእቅዱ ላይ መወያዬት እና የጋራ መግባባት ለመፍጠር ውይይት መካሄዱን ተናግረዋል።

አቶ ቢያዝን የተቋቋመው ኮሚቴ በክልል ደረጃ የጥቆማ መስጫ ሳጥኖችን አስቀምጧል ብለዋል። ሳጥኖቹ ፖሊስ ኮሚሽን፣ ፀረ-ሙስና ኮሚሽን እንዲሁም ፍትሕ ቢሮ ላይ ሳጥኖች መቀመጣቸውን ተናግረዋል። ሕዝቡም ጥቆማ ማድረግ መጀመሩን እና ጥፋተኛ በተባሉ 20 ሰዎች ላይ ክስ መመስረቱን ተናግረዋል።

እስካሁን 557 ጥቆማዎች ተደርገዋል፤ ከእነዚህ ውስጥ 400 ጥቆማዎች ላይ ፖሊስ ምርመራ አድርጎ አጣርቷል። 134 ጥቆማዎች ተጠናቀው ለፍትሕ ቢሮ ደርሰዋል። 54 ጥቆማዎችን ፍትሕ ቢሮ አጣርቶ ውሳኔ ሰጥቷል፤ በ20 ጥቆማዎች ላይ ክስ ተመሥርቷል፤ በዚህም 27 ሚሊየን ብር እና 62 ሺህ ካሬ ሜትር በላይ ቦታ እገዳ መጣሉን አብራርተዋል። ቀሪ 80 መዝገቦች የኮሚቴው ውሳኔ ስለሚያስፈልግ እየተጠባበቁ መኾኑን ተናግረዋል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ የፀረ-ሙስና ትግሉን ሁሉም ሊቀላቀል እንደሚገባ ከተለያዩ ዞኖች የመጡ የፀረ-ሙስና ኮሚቴ አባላት ተናግረዋል።

# ከሚያሽከረከረው ባጃጅ ላይ የተረሳ 150 ሺህ ብር ለባለቤቱ የመለሰው የባጃጅ አሽከርካሪ ምስጋና እየተቸረው ነው

በድሬዳዋ ከተማ ከሚያሽከረከረው ባጃጅ ላይ የተረሳ 150 ሺህ ብር ለባለቤቱ የመለሰው የባጃጅ አሽከርካሪ አድናቆት እየተቸረው ይገኛል።

መኮንን ግርማ ኑሮን ለማሸነፍ እና የነገውን ተስፋ ብሩህ ለማድረግ ባጃጅ ላይ ተቀጥሮ የሚሰራ ወጣት ነው።

ወጣቱ መጋቢት 15 ቀን 2015 ዓ.ም እንደተለመደው ለስራ በድሬዳዋ ጎዳና ላይ ከምሽቱ ሶስት ሰአት ላይ ባጃጁን እያሽከረከረ ሳለ የድሬዳዋ ከተማ ነዋሪ የሆኑት አቶ መሀመድ ዑስማን ከሳቢያን ወደ አርቢት ለመሄድ በሱ ባጃጅ ተሳፍረው ወደተባለው ቦታ ማድረሱን ተናግሯል።

ይህ ከሆነ ከአንድ ሰአት በኋላ ስልክ ተደውሎ ባጃጁ ላይ ገንዘብ ወድቆ እንደሆነ እና እንድመለከት ተነገረኝ የሚለው ወጣቱ፥ ከተሳፋሪ ወንበር ላይ ዞሬ ስመለከት በላስቲክ የተጠቀለለ በርካታ ብር ተቀምጦ ማግኘቱን እና ወዲያው ገንዘቡን ይዞ ወደ ድሬዳዋ ፖሊስ ትራፊክ ዳሬክቶሬት በመምጣት 150 ሺህ ብሩን ለባለቤቱ መመለሱን ገልጿል።

ገንዘቡን ለባለቤቱ መመለሱ እንዳስደሰተው የተናገረው ወጣቱ፣ የራስ ያልሆነ ገንዘብ ለግል መጠቀም የህሊና ቁስል በመሆኑ በራስ ወዝ ብቻ ሀብት ማፍራት እንደሚገባ መናገሩን ከድሬዳዋ ፖሊስ ያገኘነው መረጃ ያመለክታል።

ገንዘባቸው የተመለሰላቸው አቶ መሐመድ ዑስማን በበኩላቸው፤ ገንዘባቸው በጠፋ በአንድ ሰዓት ውስጥ የተሳፈሩበትን የምሽት ባጃጅ የጎን ቁጥር ለትራፊክ ፖሊስ በመናገር በፍጥነት ገንዘባቸው በመገኘቱ መደሠታቸውን ገልፀው፥ ለድሬዳዋ ትራፊክ ቁጥጥር ዳሬክቶሬት እና ለወጣት መኮንን ግርማ ምስጋናቸውን ማቅረባቸውን ኢቢሲ ዘግቧል።

ባለፈው መኪናው ውስጥ ያገኘውን 170 ሺህ ብር ዋጋ የሚገመት የወርቅ ሸዋሊያ ጌጥ ለባለቤቷ በመመለስ አርዓያነት ያለው ተግባር የፈጸመው የድሬዳዋ ነዋሪ ወጣት ናርዶስ ዳንኤል ከድሬድዋ



# በሙስና ወንጀል በተከሰሱ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኞች ላይ የቅጣት ውሳኔ ተሰጠ

የቅጣት ውሳኔውን የወሰነው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 1ኛ የሙስና ጉዳዮች ወንጀል ችሎት ሲሆን፥ የቅጣት ውሳኔ የተላለፈባቸው ተከሳሾች ዳኛ አዱኛ ነጋሳ እና ዳኛ አክሊሉ ዘሪሁን ይባላሉ።

የሙስና ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ዐቃቤ ህግ በመዝገብ ቁጥር 276ll አቶ ዳዊት ገብረእግዛብሔር በተባሉ ባለሀብት እና ቱፋ ጣፋ በተባለ ግለሰብ በነበረ የስራ ግንኙነት ሳይከፈል የቀረ 276 ሚሊየን ብር እዳ እና 9 ከመቶ ወለድ ማለትም 250 ሺህ ብር የግልግል ዳኝነት ላይ ክርክር ያልተደረገበት ማስረጃ ባልተመዘነበት ተገቢ ያልሆነ የአፈጻጸም ውሳኔ ሰጥተዋል በማለት ህዳር 28 ቀን 2014 ዓ.ም የከባድ ሙስና ወንጀል ክስ መስርቶባቸው ነበር።

ተከሳሾቹ ክሱ ከደረሳቸው በኋላ ታህሳስ 14 ቀን 2014 ዓ.ም በነበረ ቀጠሮ ወንጀሉን አለመፈጸማቸውን ገልጸው የሰጡትን የዕምነት ክህደት ቃላቸውን ተከትሎ የዐቃቤ ህግ ምስክሮች ቀርበው ተሰምተዋል።

ፍርድ ቤቱም የምስክር ቃል መርምሮ አንደኛ ተከሳሽ ዳኛ አዱኛ ነጋሳ ከቀረቡባቸው ሁለት ክሶች መካከል በህገወጥ መንገድ የተገኘን ገንዘብ ንብረት ህጋዊ አስመስሎ መጠቀም ወንጀል በሚመለከት በምስክር አልተረጋገጠም ሲል ነጻ ብሏቸው ነበር።

በሌላኛው ክስ፡- ስልጣንን ያለአግባብ መጠቀም የሙስና ወንጀል እንዲከላከሉ ሐምሌ 13 ቀን 2014 ዓ.ም ብይን ተሰጥቷል።

ሁለተኛ ተከሳሽ ዳኛ አክሊሉ ዘሪሁንን በተመለከተ በወቅቱ በተሰጠው የግልግል ዳኝነት ላይ ሀሰተኛ ሰነድ ስለመቅረቡ እንደማያውቁ በምስክር በመረጋገጡ የተከሰሱበት አንቀጽ ተቀይሮ በግል ተሰሚነት መነገድ አንቀጽ 16/1 ሀ መሰረት እንዲከላከሉ ብይን ተሰጥቶ ነበር።

ይህ አንቀጽ ዋስትናን ስለማያስከለክል በ20 ሺህ ብር ዋስ በውጭ ሆነው ጉዳያቸውን እንዲከታተሉ ዋስትና ተፈቅዶላቸውም ነበር።

ተከሳሾቹም በተለያየ ጊዜ የመከላከያ ማስረጃ ያቀረቡ ቢሆንም የዐቃቤ ህግ ማስረጃን በተገቢው ማስተባበል አልቻሉም ተብለው የጥፋተኝነት ፍርድ ተላልፎባቸዋል።

የጥፋተኝነት ፍርድ ከተላለፈባቸው በኋላ 1ኛ ተከሳሽ ዳኛ አዱኛ ከመከሰሳቸው በፊት በታማኝነት ለፍትህ ስርዓቱ ያበረከቱትን አስተዋጽኦ፣ የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆናቸውን እና ለሀገራዊ ልማት ያበረከቱትን በማስረጃ አስደግፈው አጠቃላይ 12 የቅጣት ማቅለያዎችን አቅርበዋል።

2ኛ ተከሳሽ ዳኛ አክሊሉ ዘሪሁንም ከመከሰሳቸው በፊት ለፍትህ ስርዓቱ በታማኝነት ያበረከቱትን አስተዋጾ ጠቅሰው አጠቃላይ 10 የቅጣት ማቅለያ አስተያየት በጽሁፍ አቅርበዋል።

ፍርድ ቤቱም ያቀረቡትን የቅጣት ማቅለያ አስተያየት በመያዝ 1ኛ ተከሳሽ ዳኛ አዱኛ ነጋሳን ጥፋተኛ በተባሉበት አንቀጽ በ2 ዓመት ከ9 ወር ጽኑ እስራት እንዲቀጡ እንዲሁም 2ኛ ተከሳሽ ዳኛ አክሊሉ ዘሪሁን ጥፋተኛ በተባሉበት አንቀጽ በ1 አመት ከ6 ወራት ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ተወስኗል።

# በሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ጉዳይ ላይ ግንዛቤ መፍጠር የሚያስችል የጥያቄና መልስ ውድድር ለማካሄድ የማስጀመሪያ ፕሮግራም ተካሄዳ

የፌዴራል እና የክልል እንዲሁም የከተማ አስተዳደር ተቋማት የስነምግባር እና የፀረ-ሙስና መከታተያ ክፍል ኃላፊዎችና ባለሙያዎች በስነምግባር ግንባታ እና ሙስና መከላከል ዙሪያ የጥያቄ እና መልስ ውድድር ማስጀመሪያ ፕሮግራም በኢንተር ሌግዠሪ ሆቴል ተካሄዷል።

የፌደራል የስነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ሳሙኤል ኡርቃቶ (ዶ/ር) መንግስት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ሙስና የሀገራችን የልማት ማነቆ መሆኑን በመገንዘብ ሌቦችን ተጠያቂ የማድረግ እና የህግ ማስከበር ስራ እያከናወነ መሆኑን ገልፀዋል።

ከዋልታ ሚዲያና ኮሙኒኬሽን ኮርፖሬት ጋር በጋራ በመሆን የሚዘጋጀው የጥያቄና መልስ ፕሮግራም ዓላማ ዜጎችን በማነቃቃትና ግንዛቤ በመፍጠር ለፀረ-ሙስና ትግሉ አጋዥ እንደሚሆን ገልፀዋል።

መንግስት ከመቼውም ግዜ በላይ የትኛውንም አይነት ሙስና ለመታገል ቁርጠኛ ነው ያሉት ኮሚሽነሩ፥ ሙስናን የሚጠየፍና በስነምግባር የታነፀ ትውልድ ለመፍጠር የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች ሊሰሩ ይገባል ብለዋል።

የመንግስት የስራ ኃላፊዎችም በዚህ ተግባር ላይ ሲገኙ ተጠያቂ እየሆኑ ነው የተባለ ሲሆን፣ ሰርቆ ማደር እንደማይቻል ሁሉም ሊገነዘብ ይገባል ብለዋል።

ሙስናን ለመከላከል ሁሉም የመንግስት እና የግል ተቋማት አሰራራቸውን ግልጽ በማድረግና ሌቦችን በማጋለጥ ለሀገር እድገት የበኩላቸውን ውጤት ለማምጣት አጋዥ ሊሆኑ ይገባል ብለዋል።

በሌላ መልኩ በኢትዮጵያ ባህልና ሞራል እሴት ውስጥ ሆኖ በስነምግባር የታነፁ ህፃናት እና ወጣቶች ብሎም አዋቂዎችን ግንዛቤ በመፍጠር ሙስና የመከላከል ፕሮግራም ይሆናል ብለዋል።



የዋልታ ሚዲያ ኮሙኒኬሽን ኮርፖሬት ም/ ስራ አስፈፃሚ አቶ ዘላለም እንደሻው ስለ መድረኩ ዓላማ ሲያብራሩ፥ የጥያቄና መልስ ፕሮግራሙ ህብረተሰቡ በየቤታቸው ሁነው ስለ ስነምግባር ግንባታ እና ሙስና መከላከል ግንዛቤ የሚያገኙበትና የሙስና መከላከል ስራው አጋዥ የሚሆኑበት ነው ብለዋል።

የፌደራል የስነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን የስነ-ምግባር ግንባታና የፀረ-ሙስና ባለድርሻ አካላት ማስተባበሪያ መሪ ስራ አስፈጻሚ ዴስክ ኃላፊ አቶ የውኃላእሸት ደሳለኝ ስለጥያቄና መልስ ውድድር አጠቃላይ ዓላማ በተመለከተ ማብራሪያ አቅርበዋል።

የእጣ ማውጣት ፕሮግራሙ የተካሄደ ሲሆን፤ በቀጣይ የጥያቄ እና መልስ ውድድር ፕሮግራሙ በዋልታ ሚዲያ ኮሙኒኬሽን ኮርፖሬት የቴሌቪዥን ፕሮግራም በእየሳምንቱ በቀጥታ ለተመልካች የሚተላለፍ ይሆናል።







# የኮሚሽኑ አመራሮች ከተባበሩት መንግሥታት የምሥራቅ አፍሪካ የፀረ-ሙስና እና ተያያዥ ወንጀሎች ክትትል ቢሮ (UNODC) ተወካይ ጋር ውይይት አደረጉ

የተባበሩት መንግሥታት የምሥራቅ አፍሪካ የፀረ-ሙስና እና ተያያዥ ወንጀሎች ክትትል ቢሮ ተወካይ (UNODC) በኮሚሽኑ ጉብኝት በማድረግ የዓለምአቀፉ የፀረ-ሙስና ስምምነት በኢትዮጵያ የሕግ አካል የተደረገውን፣ የትግበራ ዉጤታማነትን ለማጠናከር በሚያግዙ ጉዳዮች እንዲሁም በቀጣይ በትብብር ለመሥራት ከኮሚሽኑ አመራሮች ጋር መክረዋል።

በተለይም፣ ከኢትዮጵያ በሙስና የሚሸሹ ሀብቶችን መዳረሻዎችን መለየት እና ተጠያቂነትን ማረጋገጥ የትኩረት አቅጣጫ መሆኑን በውይይቱ ተገልጿል።

በቀጣይም በተለያዩ ጉዳዮች ላይ አብረው መስራት በሚቻልባቸው ጉዳዮች ላይ ሀሳብ መለዋወጥ ችለዋል።

በተመሳሳይ መረጃ የፌዴራል የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን አመራሮች በሥነ-ምግባር ግንባታ ዙሪያ ጥናትና ምርምር እና የልህቀት ማእከል ሆኖ ከሚሰራ አለም አቀፍ ተቋም (Global Ethics) ፕሬዘዳንት ፕሮፌሰር ቸርስቶቭ ስቶክልበርገር ጋር ለመስራት በሚያስችሉ ጉዳዮች ላይ ውይይት አድርገዋል፡፡

የፌዴራል ሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ም/ ኮሚሽነር አቶ ወዶ አጦ ኮሚሽኑ የሚያከናወናቸውን ተግባራት ለተሳታፊዎች ገለፃ አድርገዋል፡፡ የሥነ-ምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ተግባራትን በተለያዩ አማራጮች በመጠቀም ህብረተሰቡን የማስተማር ስራ ተግባራዊ እያደረገ እንደሆነ አብራርተዋል፡፡

የሥነ-ምግባር ግንባታ ተልዕኮውን ለመወጣት ኮሚሽኑ ከሃይማኖት ተቋማት፣ ሲቪክ ማህበራት እንዲሁም ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት እንደሚሰራ ገለፃ ያደረጉ ሲሆን፤ በሥነ-ምግባር ግንባታ ዙሪያ ለመስራት ፍላጎት ካለው ማንኛውም ሀገር በቀል እና ዓለም አቀፍ ተቋም ጋር በጋራ ለመስራት በሩ ክፍት እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

ፕሮፌሰር ቸርስቶቭ በሥነ-ምግባር ግንባታ ላይ በተለያዩ ሀገራት ከሚገኙ የሃይማኖት ተቋማትና ሲቪክ ማህበራት እንዲሁም ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በቅንጅት እየሰሩ እንደሚገኝ ገልፀው፤ ከኮሚሽኑ ጋር በሥነ-ምግባር ግንባታ ላይ አብረን ብንሰራ ውጤት ማምጣት እንደሚቻል አብራርተዋል፡፡

በሀገራት በሥነ-ምግባር ግንባታ ብቁ የሆነ ዜጋ አለመኖር ለሙስናና ብልሹ አሰራር ምክኒያት እየሆነ እንደሚገኝና፤ ችግሩን ለመቀነስ የሃይማኖት ተቋማትን በመጠቀም አማኙን ማህበረሰብ በሥነ-



ምግባር ግንባታ ላይ ትኩረት በማድረግ የግንዛቤ ትምህርት ቢሰጥ ዘላቂ ለውጥ ማምጣት እንደሚቻል ገልፀዋል፡፡

በውይይቱ የተገኙት የክርስትያን ተራድኦ ድርጅት ዋና ዳይሬክተር ዶ/ር ንጉሴ ለገሰ እንደገለፁት ለአንድ ሀገር እድገት በሥነ-ምግባሩ የታነፀ ትውልድ መፍጠር አስፈላጊ በመሆኑ ከኬጂ ጀምሮ የሥነ-ምግባር ትምህርት መስጠት አስፈላጊ መሆኑን ገልፀው፤ ከሃይማኖት ተቋማትና ከሲቪክ ማህበራት ጋር በቅንጅት በመስራት ሙስናና ብልሹ አሰራርን የሚፀየፍ ማህበረሰብ መፍጠር ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

በፌደራል የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን የባለድርሻ አካላት ማስተባበሪያ ስራ አስፈፃሚ አቶ ሀረጎት አብርሃ በንግግራቸው ኮሚሽኑ ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል የሥነ-ምግባር ግንባታ ላይ ትኩረት አድርጎ ከተለያዩ ሲቪክ ማህበራት እንዲሁም ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት እየሰራ መሆኑን ገልፀው፤ ከእናንተ ጋር አብረን ብንሰራ ውጤት ማምጣት እንደሚቻል እና በዚህ ዙሪያ የሚሰሩ ሲቪል ሶሳይቲዎች ቁጥራቸው አነስተኛ በመሆኑ እንዲጠናከሩ ለማድረግ ትልቅ እድል እንደሚፈጥር ገልፀዋል ፡፡

በመጨረሻም ሁለቱም ወገኖች ሥነ-ምግባር ግንባታ ላይ ትኩረት በማድረግ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ የኦንላይን ስልጠና ላይ ለመስራት በቃል ደረጃ ስምምንት ላይ የደረሱ ሲሆን፤ በቀጣይ በጉዳዩ ላይ የበሰለ ውይይት በማድረግ የፊርማ ስምምነት እንደሚያደርጉ መነጋገር ችለዋል፡፡

# ቆይታ



**የፌደራል የሥነ-ምግባር የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በህግ የተሰጠውን ሙስናን የመከላከል ተልዕኮ በአግባቡ ለመወጣት የትውልድን የሥነ-ምግባር እና የሞራል እሴቶች የመገንባት፣ በመንግስት ተቋማትና በህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ የሚስተዋሉ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች እንዲለዩና እንዲፈቱ የማድረግ፣ ሀብት መመዝገብና ትክክለኛነቱን በማረጋገጥ በተቋማት የግልፀኝነትና የተጠያቂነት ስርዓት እንዲሰፍን ማድረግና የተለያዩ ባለድርሻ አካላትንና መላውን ህብረተሰብ የፀረ-ሙስና ትግሉ ባለቤት እንዲሆን ማስቻል ሲሆን፣ ኮሚሽኑ ይህን ዓለማ አንገቦ ስራዎችን እያከናወነ ይገኛል፡፡**

የፌደራል የሥነ-ምግባር የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በህግ የተሰጠውን ሙስናን የመከላከል ተልዕኮ በአግባቡ ለመወጣት የትውልድን የሥነ-ምግባር እና የሞራል እሴቶች የመገንባት ተግባር ከግብ ለማድረስ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር (ኢመደአ) የመንግስት ተቋማት ላይ ከሕዝብ የሚቀርቡ አስተያየቶችን፣ የመልካም አስተዳደር ቅሬታዎችን እንዲሁም የሙስና ጥቆማዎችን ለመቀበል የሚያስችል ሶፍትዌር በማልማት ከፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ጋር የካቲት 24/2015 ርክክብ መደረጉ ይታወቃል::

ስለሆነም የ‹‹ፀረ-ሙስና›› ጋዜጣ የዘጠነኛ ዕትም እንግዳችን የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ዋና ዳይሬክተር የተከበሩ አቶ ሰለሞን ሶካ ናቸው:: የ‹‹ፀረ-ሙስና›› ጋዜጣ ከዋና ዳይሬክተር የተከበሩ አቶ ሰለሞን ሶካ ጋር ያደረገችውን ቆይታ ይዛ ቀርባለች:: መልካም የንባብ ጊዜ...

የ‹‹ፀረ-ሙስና›› ጋዜጣ፡- የህዝብ ግብረመልስ መስጫ ፕላትፎርሙ ሙስናን ከመዋጋት አንፃር ምን ፋይዳ ይኖረዋል?

አቶ ሰለሞን ሶካ፡- ዜጎች በተለያዩ የመንግስት ተቋማት ላይ በሚያገኟቸው አገልግሎቶች ላይ ያላቸውን አስተያየት ወይም የእርካታ መጠንና በአገልግሎት ሂደት የሚገጥማቸው የመልካም አስተዳደር ችግርን የሙስና ጥቆማ ሶፍትዌሩን በመጠቀም በየትኛውም ቦታና በፈለጉበት ሰዓት ጥቆማ ወይም አስተያየታቸውን መስጠት ያስችላል::

ከዚህ በፊት ችግር ሲያጋጥማቸው የት እና ለማን እንናገር ብለው ይፈራሉ፤ ምክኒያቱም በጣም የተደራጀ ሌብነት ስላለ እና ለበላይ አካል ሂደው ሲናገሩ ለውጥ ባለመኖሩ ዜጎች በምሬት ውስጥ ሁነው መንግስት ላይ አሜኔታ እያጡ የሄዱበት ሁኔታ ነው ያለው፤ አሁን ግን የሚሰጡት መረጃ ቀጥታ ማእከላዊ ዳታ ቤዝ ይመጣል፤ ይህን መረጃ የፌደራል የስነምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን በማየት ያጠናክረዋል፤ ጥቆማው ቀጥታ ወደ ዋናው ምንጭ ስለመጣ ዜጎችን የሚያሳስብ ነገር ይለውም ማለት ነው::

በሁለተኛ ደረጃ ዜጎች ብንናገር ጥቃት ይደርስበናል ብለው ስለሚያስቡ ጥቆማ ሲያደርጉ ከተደራጁ ሌቦች ተጋላጭ ሊሆኑ ስለሚችሉ ግለኝነታቸው የተጠበቀ እንዲሆን ያደርጋቸዋል::

ሌላው ሶፍትዌሩ በ5 ሃገርኛ ቋንቋዎች እንዲሁም በእንግሊዝኛ ቋንቋ በየትኛውም የአለም ክፍል ላይ ሁነው 24 ሰዓት አገልግሎት መስጠት ይችላል:: እንዲሁም ለአይነ ሥውራን ዜጎች ምቹ በሆነ መልኩ በድምጽ ታግዘው አገልግሎቱን ማግኘት እንዲችሉ ተደርጎ አገልግሎት የሚሰጥ ሶፍትዌር በመሆኑ ጠቀሜታው የጎላ ይሆናል::

የ‹‹ፀረ-ሙስና›› ጋዜጣ፡- ሶፍት ዌሩ ለኮሚሽኑ ብሎም ለሌሎች ተቋማት ጠቀሜታው ምንድን ነው?

አቶ ሰለሞን ሶካ፡- ሶፍትዌሩ የኮሚሽኑን ሥራ ከማቀላጠፍ አኳያ ጥቆማዎችን ለመቀበል ያወጣ የነበረውን ገንዘብና ጊዜ በማስቀረት፣ ሕብረተሰቡ ያልተገደበ ተሳትፎ እንዲኖረው በማድረግ እንዲሁም ሕብረተሰቡ የሚሰጣቸውን ጥቆማዎች በቀጥታ የትኛውም ሦስተኛ ወገን ሳይነካካው ለማግኘት ይረዳዋል::

የመንግስት ተቋማት ለህዝብ መስጠት ያለባቸውን አገልግሎት በአግባቡ እንዲሰጡ የሚያበረታታ ስርዓት ነው፤ እንደዚሁም ብልሹ አሰራር ያለባቸውን ተቋማት ራሳቸውን በመስታውት እንዲያዩ እና ምን አይነት የመልካም አስተዳደርና ብልሹ አሰራር እንዳለ እና ምን አይነት ሌቦች ተቋማት ውስጥ ተሰግስገው ይገኛሉ

**የቢሔራዊ ደህንነት ስጋት የሆነውን ሙስናና ብልሹ አሰራር ከመታገል አንፃር ህብረተሰቡ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆን የሚያስችል የሙስና እና የመልካም አስተዳደር ችግሮች መቀበያ ሶፍትዌር በማልማት ለፌዴራል የሥነ ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን አስረክበናል። ይህም “የሕዝብ አስተያየት መቀበያ ሲስተም - Public Feedback System” የሚል መጠሪያ ስያሜ ያለው ሲሆን፤ ማንኛውም የሕብረተሰብ ክፍል የሶፍትዌሩን ዌብሳይት አድራሻ https://epfs.gov.et በመጠቀም አገልግሎቱን ማግኘት ይችላል**



የሚለውን የሚያዩበት ነው::

በተመሳሳይ ህብረተሰቡ በመልካም አስተዳደር እጦት ችግር መስተጓጎል ሊገጥው ይችላል፤ ብሎም አገልግሎቱን ለማግኘት ያልተፈለገ ክፍያ ወይም ሌቦች ሙስና የሚባለውን ነገር ሊጠይቁ ይችላል:: በተቃራኒው ዜጎች አገልግሎቱን በአግባቡ ተስተናግደው ሊመለሱ ይችላል:: ስለሆነም ይህ ሲስተም ተቋማት በዜጎች ዘንድ ያላቸውን ምልከታ ያዩበታል፤ መልካም አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም ጎበዝ መሆናቸው በተጨባጭ በህዝብ ዘንድ ታምኖበት እንዲጨበጨብለት ይሆናል:: በሌላ መልኩ ህዝብን የሚጓትትና ብልሹ አሰራርና በመልካም አስተዳደር እጦት እና ሌብነት የሚሰሩ ተቋማት በህዝብ ዘንድ ምን አይነት ምልከታ እንዳላቸው ራሳቸውን የሚያዩበት ይሆናል::

የ‹‹ፀረ-ሙስና›› ጋዜጣ፡- ሙስና ውስብስብ ከመሆኑ አንፃር ጥቆማ የሚሰጡ ሰዎች ደህንነታው በምን ልክ ይጠበቃል?

አቶ ሰለሞን ሶካ፡- መረጃው ያልተፈለገ ሰው እጅ ላይ እንዳይደርስ ተቋማችን ልዩ ጥበቃ የሚያደርግ ይሆናል፤ በተለይ ይሄ የብሄራዊ ደህንነት ስጋት ተብሎ የተለየው ብልሹ አሰራርና ሌብነት እኛ ልዩ ትኩረት በመስጠት የምንሰራበት ይሆናል:: ህብረተሰቡን ቀረብ ብለን ያለ ስጋት ደህንነቱ ተጠብቆ ግላዊ ከለላ አግንተው በነፃነት የፈለገውን መረጃ በመጠቆምና አስተያየታቸውን እንዲሁም ቅሬታቸውን እንዲያቀርቡ የሚያስችል የተዘረጋ ስርዓት ነው::

ይህ የሚቀርበው ቅሬታና አስተያየት ብሎም ጥቆማ ግለሰቦች ላይ አሉታዊ ተፅኖ ሊያደርስባቸው ይችላል:: ስለዚህ ችግሩ እንዳይደርስባቸው ሲስተሙን የመጠበቅ ኃላፊነት ተቋሙ አለበት፤ ይህ 24 ሰባት የሚሰራው የተቋሙ የሳይበር ሰራዊት ሲስተሙን ዘብ ሁኖ ስለሚጠብቅ ዜጎች ስጋት ሊገባቸው አይችልም::

የ‹‹ፀረ-ሙስና›› ጋዜጣ፡- የተከበሩ አቶ ሰለሞን ሶካ በመጨረሻ ለአንባቢያን የሚያስተላልፉት መልክት ይኖር ይሆን?

አቶ ሰለሞን ሶካ፡- ኢመደአ ሃገራዊ የእውቀትና የቴክኖሎጂ ባለቤትነትን በማረጋገጥ ሂደት የሚያለማቸውን ቴክኖሎጂዎች ለተለያዩ የመንግስት ተቋማት እንሰጣለን::

የብሔራዊ ደህንነት ስጋት የሆነውን ሙስና ከመታገል አንፃር ሕብረተሰቡ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆን የሚያስችል የሙስና እና የመልካም አስተዳደር ችግሮች መቀበያ ሶፍትዌር በማልማት ለፌዴራል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን አስረክበናል::

ይህ ሶፍትዌሩ ከኮምፒውተር በተጨማሪ የሞባይል አፕሊኬሽንም ስለተሰራለት ሕብረተሰቡ በቀላሉ ከአፕ ስቶር ወይም ፕሌይ ስቶር በማውረድ መጠቀም ይችላል:: በማንኛውም የመንግስት ተቋማት ላይ የሚቀርቡ የሕዝብ አስተያየቶችን፣ የመልካም አስተዳደር ቅሬታዎችን፣ እንዲሁም የሙስና ጥቆማዎችን ለመቀበል የሚያስችል አገልግሎቶች ያለው ሶፍትዌር ነው:: ሶፍትዌሩ “የሕዝብ አስተያየት መቀበያ ሲስተም - Public Feedback System” የሚል መጠሪያ ስያሜ ያለው ሲሆን፤ ማንኛውም የሕብረተሰብ ክፍል የሶፍትዌሩን ዌብሳይት አድራሻ https://epfs.gov.et በመጠቀም አገልግሎቱን ማግኘት ይችላል::

ስለዚህ ህብረተሰቡ ምቹ የሚሉት ቦታ እና የኔትወርክ አክሰስ የሚያገኙበት ቦታ በነፃነት የሚፈልጉትን አይነት ጥቆማም ሆነ አስተያየት እንዲሁም ቅሬታ ማቅረብ እንዲችሉ ትልቅ እድል ይፈጥራል ማለት ነው::

ይህንን የሙስና ጥቆማ መቀበያ ሶፍትዌር ሕብረተሰቡ በአግባቡ እንዲጠቀምና ሃገራዊ የሙስና ትግሉን መደገፍ ይኖርበታል በማለት መልክት አስተላልፈዋል::

# ሳይቃጠል በቅጠል

## ለጠንካራ የፀረ-ሙስና ትግል ጠንካራ ተቋማዊ አደረጃጀት እና አሰራር ያስፈልጋል

**ተስፋዬ ሻሜቦ**

ሙስና የራስ ያልሆነውን የመንግስትና የሕዝብ ሀብት ያለአልግባብ ለግል ጥቅማ ማዋል እንደሆነ ብዙዎች ይሰማሙበታል:: ሰዎች በውስጣቸው ባለው የአመላከከት ችግር ወይም ሙስና እንዲፈጸም በሚፈጠረው የሰዎች ወይም የሁኔታዎች (በቤተሰብ ጭምር) ግፊት ወይም ሙስና ለመሥራት ምቹ ሁኔታዎችና አጋጣሚዎች (በህጎች ክፍተትና ቁጥጥር መላለት) ሲኖሩ ሙስና ይሰራሉ::

ሙስና የሚሰራው በግለሰብ ደረጃ በተናጠል ወይም በቡድን በመደራጀት ሊሆን ይችላል::ሙስና መንግስታዊና መንግስታዊ በሆኑ ተቋማት ውስጥ የሚሠራ ሲሆን፥ ከተራ ሰራተኛ እስከ የተቋም የበላይ ኃላፊ የተባለው ድረስ ሊሠራበት ይችላል:: በሙስና ገቢ በጣም ጥቂት የሆኑ ግለሰቦች የተንደላቀቀ ኑሮ ሲኖሩ፥ ብዙሃኑ ህዝብ በድህነት ውስጥ እንዲኖር የሚያደርግ ወንጀል ሲሆን በሀገር ደረጃ የኢኮኖሚና የልማት ዕድገትን የሚያቀጭጭ ተግባርም ነው::

ሙስና በየጊዜው መልኩን ስለሚቀያይር ማጥፋት አይቻልም፤ ነገር ግን ሙስና በሚሠሩ ሰዎች ላይ ጠንካራ የቅጣት ውሳኔ በመበየንና ያንኑ ለሌሎች በማስተመሪያነት በመጠቀም፣ በተቋም ውስጥ አሰራሮችን በማዘመን፣ የሚከናወኑ ተግባራት በአንድ ግለሰብ ብቻ እንዳይወሰን የሚና ክፍፍል በማድረግና አንዱ የሠራውን ሌለው የሚያረጋግጥበት ጠንካራ ሥርዓት ተግባራዊ በማድረግ፣ የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት በማጠናከር ወዘተ መቀነስ ይቻላል:: የሚወጡ ህጎችና ደንቦች፣ የሚዘጋጁ መመሪያዎችን ሙስናን ለመሥራት እንደማይመቹ በማድረግም ሆነ ወቅታዊነትን በመጠበቅ ሙስና መከላከል ይቻላል:: ሰዎች ወደ ሙስና እንዳይገቡና እንዲቆጠቡ በተደጋገሚ የአመለካከት ለውጥ የሚያመጣ የሥነ-ምግባርና የግብረገብ ትምህርት በማስተማር ሙስናን መቀነስ ይቻላል::

ስለ ሙስና ይህን ያህል ካልን ሙስናን በሀገር ደረጃ ለመታገል ምን ዓይነት የፀረ-ሙስና ተቋም ማቋቋም ያስፈልጋል የሚለውን ማየት ያስፈልጋል::

በደሃ ሀገራት የይስሙላ የፀረ-ሙስና ተቋምን እንደሚያቋቋሙ መረጃዎች ያመለክታሉ፤ ደሃ ሀገራት የፀረ-ሙስና ተቋምን አባዳሪና ለጋሽ ድርጅቶች ብድርና ዕርዳታ ለመስጠት ተቋሙን እንደ አንድ መሥፈርት ስለሚወስዱ ይህንኑ ለማሟላት ብቻ እንደሚያቋቋሙም ጥናቶች ይገለፃሉ:: ስለሆም ለፀረ-ሙስና ትግሉ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር አይፈልጉም:: ለተቋሙ ሥራ በቂ በጀት አይመድቡም:: የፀረ-ሙስና ትግል ልዩ የሙያ ክህሎትን የሚጠይቅ ቢሆንም በዘርፉ ልምድና ዕውቀት ያላቸው ባለሙያዎች እንዲኖር አይፈለግም:: ተቋሙን ከሌሎች መንግስታዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ለይተው አያዩትም:: የፀረ-ሙስና ተቋም ሙስና የመከላከል ሥራ ላይ ጠንክሮ በመሥራት በሀገሪቱ የፀረ-ሙስና ትግሉ ላይ ውጤት እንዲታይ ብዙም አይፈለግም:: በተለምዶ ጥርስ የሌለው አንበሰ የሚባሉ የፀረ-ሙስና ተቋማትን ያደራጃሉ:: ይህም የሀገሪቱን የፀረ-ሙስና ትግል ውጤት አልባ እንዲሆን ያደርጋል::

ሌላው በፀረ-ሙስና ተቋማት የሚፈጸም ጥቃት ነው:: አንዳንድ ደሃ ሀገራት ከመንግስት አስተዳደር ውስጥ የሚያፈነግጡ ሰዎችን የሙስና ተጠርጣሪ ታፔላ በመለጠፍ በህግ ጥላ ሥር እንዲሆን ያደርጉታል:: የፀረ-ሙስና ተቋምን እንደሚጮህ ውሻ ጃስ እያሉ በአፈንጋጮች ላይ በፀረ-ሙስና ተቋም በኩል ጡንቻቸውን ያሳርፉበታል::



ፀረ-ሙስና ተቋሙም ሰዎችን ያለ ጥፋታቸው ያስራል፣ የተጭበረበረና የሀሰተኛ ሠነድ ይከሳል፣ ያስቀጣል:: ይህ ሁለተኛው የውጤት አልባነት ምክንያት ተደርጎ ይወሰዳል::

ከማንኛውን አካል ነፃና ገለልተኛ የሆነ ፀረ-ሙስና ተቋም ሌላው ዓይነት ነው:: ይህ ተቋም ከማንኛውም አካል ነፃና ገለልተኛ ሆኖ የሚያገልግል እንደመሆኑ መጠን የሙስና ወንጀል ጥቆማዎችን በገለልተኝነት ይቀበላል፤ ከዜጎች የቀረቡ ጥቆማዎች አንዳችም ሳይባክኑ በገለለተኝነት ይመረምራል፣ ይከሳል፣ ያስቀጣል:: በሙስና የተመዘበረ ሀብት ያስመልሳል፣ በመረጃና ማስረጃ ላይ የተመሰረተ ምርመራ ስለሚያካሄድ ሰዎችን ያለጥፈታቸው እንዲከሰሱ አያደርግም:: ከተራ ዜጋና ሰራተኛ እስከ ከፍተኛ የመንግስት ኃላፊ ድረስ ሙስና እስከሠሩ ድረስ ያለምንም ማመንታት በግልጽነትና በተጨባጭ መረጃ ይመራምራል፤ የተከናወኑ የፀረ-ሙስና ተግባራት ውጤት በግልጽ ለህዝብ ያሳውቃል::

ይህ ውጤታማና ግንባር ቀደም የፀረ-ሙስና ተቋም ተደርጎ ይወሰዳል:: እነዚህ የፀረ-ሙስና ተቋማት ከፍተኛ የህዝብ አመኔታ ያላቸው ህዝቡም እንዳይነኩ ከለላ የሚሰጣቸው ተቋማት ናቸው::

በዓለም ላይ የፀረ-ሙስና ተቋማት አደረጃጀት ወጥ ባይሆንም ሲጠቀላል ሶስት ዓይነት ናቸው::

የመጀመሪያ የሙስና ወንጀል መመርመርና መክሰስ ላይ ትኩረት አድርጎ የሚሠራ ነው::

የሙስና ወንጀል ጥቆማዎችን ከህዝብ ይቀበላል፣ ይመራምራል፣ ይከሳል፣ ያስቀጣል፣ በሙስና የተመዘበረ ሀብት ያስመልሳል:: ተቋሙ ሙስና ወንጀሎችን ማስቀጣት ላይ ትኩረት ስለሚሰጥ ለሙስና እና ብልሹ አሰራር መከላከል ሆነ ለሥነምግባር ግንባታ ሥራ ትኩረት አይሰጥም::

ሁለተኛው አደረጃጀት የሙስና መከላከል ላይ ትኩረት አድርገው የሚንቀሳቀሱ ተቋማት ናቸው::

ለሙስና መከላከል ትኩረት የሚሰጡ ሀገራት በኢኮኖሚ ያደጉና የመጠቀ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ የሆኑ ናቸው:: ሀገራቱ የፀረ-ሙስና ተቋማት የፀረ-ሙስና ፖሊስና ስትራቴጂ ነድፈው ተግባራዊነትን ይከታተላሉ:: እንዲሁም በተቋማት የሙስና ሥጋት የሆኑ አሰራሮችንና አደረጃጀቶችን በጥናት የማሻሻል፣ የባለሥልጣናትና የሚመለከታተቸውን ሠራተኞች የሀብት ማሳወቅና ምዝገባ እንዲሁም የሀብት ምዝገባ መረጃ ትክክለኛነት የማረጋገጥ ሥራ ላይ ትኩረት አድርገው ይንቀሳቀሰሉ:: የሙስና ወንጀል ድርጊቶች ሲያገጥሙ ድርጊቶችን በፖሊስና በዐቃቤ ህግ የማስከበር ሥራ ይሰራል::

ሶስተኛው የሙስና መከላከልና የምርመራ ክስ ሥራዎችን በማጣመር የሚንቀሳቀሱ ሀገራት ናቸው::

የእነዚህ ሀገራት የፀረ-ሙስና ተቋማት የሥነ-ምግባርና የሞራል እሴት ትምህርቶችን ይሰጣሉ:: የተቋማት የሙስና ሥጋት የሆኑ አሠራሮችንና አደረጃጀቶችን በጥናት የማሻሻል፣ የሀብት ማሳወቅና ምዝገባ ሥራዎችን፣ የተመዘገበ ሀብት መረጃ ትክክለኛነትን የማረጋገጥ እንዲሁም የጥቅም ግጭት የመከላከል ሥራዎችን ይሰራሉ::

ከዚያ ባለፈ ደግሞ የሙስና ወንጀል ጥቆማዎችን በመመርመር፣ በመክሰስ፣ በማስቀጣት የተመዘበረ ሀብት የማስመለስ ሥራዎችን ይሠራሉ::

ሶስተኛውን አደረጃጀት ተግባራዊ የሚያደርጉት በአብዛኛው ደሃ ወይም በማደግ ላይ ያሉ ሀገራት ሲሆን፥ በእነዚህ ሀገራት ሙስና ብሄራዊ ችግር እንደሆነ ይገመታል:: ሙስና የሀገሪቱ ብሔራዊ ችግር በመሆኑ የአመለካከት ለውጥ የሚያመጡ ሥልጠናዎችን በጥራት ይሰጣሉ:: ተቋማት ውስጥ ለሙስና መከሰት ምክንያት የሚሆኑ አሠራሮችን እንዲሻሻሉ ትኩረት ሰጥተው ይሰራሉ:: በሁለቱም አቅጣጫ በማለፍ ሙስና የሚፈጸሙ ሰዎችን ለህግ በማቅረብ አስተማሪ የሆነ ቅጣት እንዲያገኙ ይደረጋል::

ሌላው የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ተጠሪነት ጉዳይ ነው::

በአንዳንድ ሀገራት የፀረ-ሙስና ተቋማት ለሀገሪቱ ፕሬዝዳንት ሲሆን፥ ለጠቅላይ ሚኒስቴር ተጠሪ የሚሆኑም አሉ:: ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ወይም በቀጥታ ተጠሪነት ለህዝብ የሆኑ የፀረ-ሙስና ተቋማትም በርካታ ናቸው:: ብዙውን ጊዜ ተጠሪነታቸው ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ወይም ለህዝብ የሆኑ የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ተቋማት ውጤታማ እንደሚሆኑ ጥናቶች ይገልፃሉ::

ለዚህ ምክንያቱ የነፃነትና ገለልተኝነት ጉዳይ እንደሆነም ይገልፃሉ:: በጣም ጥቂት ሀገራት ውስጥ ለፍትህ ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ (ለምሳሌ ሩሲያ) አሉ:: የሥነ-ምግባር ግንባታና የሙስና መከላከል ሥራዎች በተቋማት ውስጥ የሚያከናወኑት የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች አደራጅተው ከሚያንቀሳቀሱ አሜሪካን ጨምሮ በርካታ አገራት አሉ::

አሜሪካን ሀገር በየተቋማቱ የአመራርና ሠራተኞችን ሥነ-ምግባር ሁኔታ የሚከታተሉ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች በየተቋማቱ የተደራጁ ሲሆን፤ አንድ ተቋም ውስጥ አዲስ የሚቀጠር ሠራተኛ ሥራ ከመጀመሩ በፊት የሥነምግባር ግንባታ ሥልጠና መውሰድ ግዴታ ያደርጉታል::

ይህ የሥነምግባር ግንባታ በየሁለት አመት የሚከለስ ሲሆን ሠራተኞችና አመራሮችን ሥልጠናውን እንደ ግዴታ ተቀብለው ሥልጠናን ይወስዳሉ:: ሥልጠናውን ያልወሰዱ አመራርና ሠራተኞች የገንዘብ ቅጣትም ይጣልባቸዋል::

በአፍሪካ ናይጄሪያን ጨምሮ ኢስያ ሀገራት ውስጥ የሙስና መከላከል ሥራ ተቋማዊ ነው:: ተቋማት ይህን ለመተግበር በህግ ማዕቀፍ ይገደዳሉ:: ስለሆነም መንግስታዊና የግል ዘርፍ ተቋማት ለሙስና ሥጋት የሆኑ አሰራሮችን በመለየት ደረጃ ይሰጣሉ:: በተሰጠው ደረጃ መሠረት ለእያንዳንዱ የሙስና ሥጋት ላለባቸው አሰራሮች የማሻሻያ ዕቅድ ያቅዳሉ፤ በማሻሻያ ዕቅዱ መሠረት የሙስና ሥጋት ቅነሳ ስትራቴጂ በመንደፍ ተግባራዊ ያደርጋሉ:: የፀረ-ሙስና ተቋማት በተቋማት ቀርፀው ተግባራዊ ያደረጉት የሙስና መከላከል ተግባራት ውጤታማ መሆኑን በክትትልና ግምገማ ያረጋግጣሉ:: የሀገሬው ህዝብም በተቋማት ሙስና መከላከል ሥራ ያላቸው ሚና በጣም ከፍተኛ ነው:: የሙስና ወንጀል በግልጽነት ይጠቁማሉ::

በእነዚህ ሀገራት ወጣቶች የሥነምግባር ግንባታ ትምህርት ከመዋዕለ ህፃናት እስከ ዩኒቨርስቲ ሥርዓተ ትምህርት እንደየደረጃው ቀርፀው ትምህርት የሚሰጡ ሲሆን፤ ትምህርት ጨርሰው ወደ ሥራ ዓለም ውስጥ ለመግባትም የሥነምግባር ብቃትና ተገቢነት ማረጋገጫ እንዲወስዱ ይደረጋል:: የተቀመጠውን የብቃት ምዘና መሥፈርት ያላሟሉ ዳግም እንዲወስዱ

ሳይቃጠል በቅጠል ... ወደ ገጽ 11 የዞረ

# ከሙስና ምርመራ ዘገባ ማህደር



በዚህ ዓምድ የተለያዩ ከሙስናና ብልሹ አሠራር አንፃር በሀገር አቀፍ ደረጃ የተከናወኑና ለህብረተሰቡ ከፍተኛ እውቀትና እውነተኛ መረጃ ይሰጣሉ ተብለው የሚታመኑና በሙስና ወንጀል የተመዘበረ የሀገር፣ የህዝብና የመንግስት ሀብት በማስመለስ ዙሪያ የተሰሩ ስራዎችንና ግንዛቤ የሚፈጠርበት እንዲሁም ሀገራችን ያፀደቀቻቸውንና እየተገበረች ያለቻቸውን የተለያዩ ዓለም ዓቀፍ፣ አህጉር ዓቀፍና ቀጠና ዓቀፍ ህጎችና አፈፃፀማቸውን አስመልክቶ የተሰሩና በመሥራት ላይ ያሉ ዋና ዋና ተግባራት አጠር ተደርገው የሚቀርቡበት ነው::

## የፀረ-ሙስና ኮሚቴ የስራ እንቅስቃሴ

ሙስና በአለም አቀፍ ደረጃ ውስብስብ እና ከፍተኛ ስጋት የሚደቅን ያልተቋረጠ ትግል የሚጠይቅ ችግር ነው:: ይህን ችግር ለመቅረፍ ወይም ለመዋጋት ሀገራት በፀረ-ሙስና እና በወንጀል ፍትህ አስተዳደር ፖሊሲዎቻቸው ውስጥ በማስቀመጥ እና የህግ ማዕቀፎችን በማውጣት ሲዋጉ ይታያል::

ሀገራችን ኢትዮጵያም ሙስናን ለመዋጋት በተለያዩ ጊዜያት የተለያዩ ህጎችን በማውጣትና አደራጃጀቶችን በመፍጠር እየተንቀሳቀሰች እንደምትገኝ ይታወቃል:: በዚህ ረገድ ሙስና ያለበትን ደረጃ በማጥናት ችግሩን ለመዋጋት ሀገር አቀፍ ብሔራዊ የፀረ-ሙስና ኮሚቴ በየደረጃው በማደራጀት ላለፉት ወራቶች ስራዎች ሲሰሩ ቆይተዋል:: በመሆኑም በየደረጃው ባሉ የፀረ-ሙስና ኮሚቴ የተከናወኑ ተግባራት ከዚህ በታች እንደሚከተለው ተጠናቅሮ ቀርቧል::

### 1. የቀረቡ ጥቆማዎችን በሚመለከት

በፌደራል 759 ጥቆማዎች የቀረቡ ሲሆን 161 ከተቋማት የመጡ መሆናቸውን ለመረዳት ተችሏል:: በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የተዋቀረው ፀረ-ሙስና ኮሚቴ 90 ጥቋማዎችን የተቀበለ ሲሆን፤ የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የፀረ-ሙስና ኮሚቴ ለፖሊስ የቀረበን ጨምሮ 540 ጥቆማዎችን ተቀብሏል:: በኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት 204 ጥቆማዎች፣ ደቡብ ብሔር ብሄረሰቦች ክልላዊ መንግስት 102 ጥቆማዎች፣ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ 72 ጥቆማዎች፣ ቤንሻንጉል ጉሙዝ 70 ጥቆማዎች፣ የሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት 417 ጥቆማዎች የቀረቡ ሲሆን፣ 17 ጥቆማዎች ተገቢነት የሌላቸው መሆናቸውን ኮሚቴው አስገንዝቧል:: በተጨማሪም በሐረሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንገስት 38፣ ሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት 80፣ የጋምቤላ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት 13፣ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር 216፣ ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር 15፣ በድምሩ 2,616 ጥቆማዎች መቅረባቸውን የኮሚቴ መረጃዎች ያመለክታሉ::

### 2. ጥቆማ የቀረበባቸው የትኩረት አካባቢዎች

ከመሬት፣ ከካሳ ክፍያ፣ ከመንግስት ቤት፣ ፋይናንስ፣ ገቢዎች፣ ግዥ እና አገልግሎት አሰጣጥ ጋር በተያያዘ ስልጣንን አላግባብ በመጠቀም ገንዘብ መቀበል፤ መሬት ወረራ፣ ከመንግስት ግዥና ኮንትራት አስተዳደር፣ የመንግስት ገንዘብ ምዝበራ፣ ምንጩ ያልታወቀ ኃብትና ንብረት ማፍራት፣ ህገወጥ ካሳ ክፍያ፣ ኮንትሮባንድ ንግድና ሕገወጥ ገንዘብ ዝውውር እና የመንግስት ገቢ መሰወርና የመሳሰሉት ይገኙበታል::

### 3. ምርመራ የተደረገባቸው ጉዳዮች

በፌደራል ደረጃ 175 መዛግብት ምርመራ የተደረገባቸው ሲሆን፤ ከነዚህ ውስጥ ምርመራቸው ተጠናቆ የተደራጁ መዝገቦች 81 ናቸው:: ሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት 36 መዛግብት ላይ ምርመራ ቢደረግም የተጠናቀቁ መዝገቦች አለመኖራቸውን ግንዛቤ ተወስዷል:: አማራ ክልል 405 መዛግብት ላይ ምርመራ ተደርጎ 134 ተጠናቆ የተደራጁ መዝገቦች ናቸው:: እንዲሁም በኦሮሚያ ክልል 302 መዝገቦች ምርመራ ተደርጎባቸው 197 መጠናቀቅ ችለዋል:: በደቡብ 8 ምርመራ ተደርጎ 4 የተጠናቀቀ ሲሆን፤ ደቡብ ምዕራብ ክልል 28 ምርመራ ተደርጎ 7 ተጠናቋል:: በተመሳሳይ በቤንሻንጉል ክልል 52 መዛግብት ምርመራ ተካሂዶ 8 የተጠናቀቀ ሲሆን፤ በሀረሪ 16 ምርመራ ተካሂዶ 8 የተደራጁ መዝገቦች እንደሆኑ በሪፖርት ተጠቀሷል:: ሲዳማ ክልል 44 መዛግብት ምርመራ ተካሂዶ ሁሉም የተጠናቀቀበት አግባብ የሚበረታታ ተግባር ነው:: ጋምቤላ 6 ምርመራ ተካሂዶ 2 መዛግብት የተጠናቀቀ ሲሆን፤ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር 98 መዛግብት ላይ ምርመራ ተካሂዶ 74 መዛግብት ማጠናቀቅ ተችሏል::

በአንጻሩ ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር እና የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የፀረ-ሙስና ኮሚቴ ይህ መረጃ አስተጠናከረበት ጊዜ የተከናወነ ተግባር የለም::

### 4. ክስ የተመሰረተባቸው መዝገቦችን በተመለከተ

ከተጠናቀቁ መዝገቦች መካከል ክስ የተመሰረተባቸው በፌደራል 65፣ አማራ 4፣ ኦሮሚያ 136 ደቡብ 3፣ ደቡብ ምዕራብ 2፣ ቤንሻንጉል 1፣ ሶማሌ 124፣ ሀረሪ 8፣ ሲዳማ 30፣ ጋምቤላ 1 እንዲሁም አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር 2 መዝገቦች ናቸው:: በእነዚህ መዝገቦች በድምሩ 1,643 ተጠርጣሪዎች የተከሰሱ ሲሆን፤ ከነዚህም መካከል በኦሮሚያ 738 እንዲሁም በፌደራል 640 ተጠርጣሪዎች ላይ ክስ ተመስርቷል:: ከዚህም በተጨማሪ 2.2 ቢሊዮን ብር፣ 38 ቤቶች እንዲሁም 225,885 ሺህ ካሬ ሜትር ቦታ በምርመራ ላይ ይገኛል::

ኮሚቴው እነዚህን ተግባራት ሲያከናውን የተለያዩ ተግዳሮቶች ያገጠሙት ሲሆን፤ ከነዚህም መካከል ከተለያየ ተቋም በመወከሉ ስራውን በፍጥነት ለመስራት አለመቻል፣ የጥቆማ ማነስ፣ በተደራጀ መልኩ የሚዲያ ቅስቀሳ ያለመኖር፣ የሚቀርቡ ጥቆማዎች የሙስና ወንጀልን የሚመለከቱ አለመሆን፣ የማህበረሰቡ ተሳትፎ አናሳ መሆን፣ የምርመራ መዘግየት እና የስራ መደራረብ የሚሉት ይገኙበታል:: የተጠቀሱ ችግሮችን በመቋቋም በቀጣይ የተጠናከረ ስራ እንደሚከናወን አቅጣጫ ተቀምጧል::

በሌላ የሙስና መረጃ መኮንን አሊ የተባለው ግለሰብ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ አስተዳደር የወረዳ 2 ንግድ ፅ/ቤት ሃላፊ ሲሆን፤ በሙስና ወንጀል ተጠርጥሮ በቁጥጥር ስር የዋለው የካቲት 30 ቀን 2015 ዓ/ም ነው::

የአዲስ አበባ ፖሊስ እንዳስታወቀው አቶ ሲሳይ ገ/ፃዲቅ የተባሉት ግለሰብ የንግድ ፈቃድ ለማሳደስ ወደ ወረዳው በሄዱበት ወቅት የንግድ ፅ/ቤቱ ሃላፊ መኮንን አሊ የንግድ ፈቃዱ የዕድሳት ጊዜው ያለፈበት መሆኑን ሰበብ በማድረግ ከ1 ወር በኋላ እንደሚታደስላቸው እና ለዚህም 50 ሺህ ብር ጉቦ እንዲሰጡት ይጠይቃቸዋል::

የግል ተበዳይ ግን የተጠየቁትን ገንዘብ የመክፈል አቅም እንደሌላቸው ሲነግሩት 45ሺህ ብር እንዲሰጡት ያግባባቸው ቢሆንም መብቴን በገንዘብ አልገዛም ብለው ሁኔታውን ለፖሊስ በማሳወቃቸው ተጠርጣሪው በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከተማ ወረዳ 2 ልዩ ቦታው ሚካኤል ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ብሩን ሲቀበል በ/ከተማው ፖሊስ መምሪያ አባላት እጅ ከፍንጅ እንዲያዝ ማድረጋቸውን እና ምርመራ እየተጣራ መሆኑ ተመላክቷል::

ሙስናን ለመዋጋት እና ህብረተሰቡን ለምሬት የሚዳርጉ የአሰራር ችግሮችን ለማስወገድ እየታየ ያለው የህዝብ ተሳትፎ ውጤት እያስገኘ መሆኑን የጠቀሰው የአዲስ አበባ ፖሊስ፤ የስራ ሃላፊነታቸውን ያለ አግባብ በመጠቀም በነፃ አገልግሎት የማግኘት መብትን በገንዘብ በመሸጥ ህብረተሰቡ እንዲማረር የሚያደርጉ የመንግስት ሰራተኞችን እና የስራ ሃላፊዎችን ተከታትሎ በመያዝ በህግ እንዲጠየቁ የማድረጉ ስራ ተጠናክሮ ይቀጥላል::

በተመሳሳይ መረጃ በኢፌዲሪ ፍትሕ ሚኒስቴር የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ዘርፍ የሙስና ወንጀል ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጀነራል ዐቃቤ ሕግ ትክክለኛ ያልሆነ የበር መውጫ ወረቀት በማዘጋጀት የሚጠብቁትን ንብረት በተሽከርካሪ በማስጫን ይዘው ከግቢ ሊወጡ ሲሉ በቁጥጥር ስር በዋሉት የአዲስ አበባ ቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን ፕሮጀክት ጽ/ቤት ንብረት አስተዳደር ባለሙያውና ተባባሪው ላይ በፈፀሙት በሥራ ተግባር የሚፈጸም የመውሰድና መሰወር ከባድ የሙስና ወንጀል ክስ ተመሰረተባቸው::

ተከሳሾች ታደሰ ሽፈራው እና ሞላ ይርጋ በ1996 ዓ.ም የወጣውን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ወንጀል ህግ አንቀጽ 32(ሀ)፣ 33 እና የሙስና ወንጀሎችን ለመደንገግ የወጣውን አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀፅ 15(1)(ለ) እና (2) ላይ የተመለከተውን በመተላለፋቸው ነው ክሱ የቀረበባቸው::

የዐቃቤ ሕግ የክስ መዝገብ እንደሚያስረዳው 1ኛ ተከሳሽ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን ፕሮጀክት ሁለት ቤቶች ልማት ጽ/ቤት ንብረት አስተዳደር ባለሙያነት፣ 2ኛ ተከሳሽ ሞገስ ብርቱካን እና ጓደኞቹ የጥበቃ ኤጀንሲ ውስጥ ሽፍት መሪ ሆነው ተመድበው ሲሰሩ ተገቢ ያልሆነ ቁሳዊ ጥቅም ለማግኘት በማሳብ 1ኛ ተከሳሽ በስራው ኃላፊነት የሚጠብቀውን ንብረትነቱ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን ፕሮጀክት ሁለት ቤቶች ልማት ጽ/ቤት የሆነውን ባለ 10 ዲያሜትር ብዛት 2 ሺ 598 ቤርጋ የዋጋ ግምቱ 2 ሚሊዮን 376 ሺ 619 ብር የሆነ የአርማታ ብረት የካቲት 9 ቀን 2015 ዓ.ም በለሚ ኩራ ክ/ከተማ ወረዳ 03 አያት አርባ ዘጠኝ ተብሎ ከሚጠራው አከባቢ በኮርፖሬሽን ፕሮጀክቱ ጽ/ቤት ንብረት ክፍል ውስጥ ተቀምጦ የነበረው ብረት ውስጥ 1ኛ ተከሳሽ በየካቲት 2 ቀን 2014 ተረካቢ አንዱአለም የህንጻ ተቋራጭ ድርጅት የሚል ብዛቱ 446 ኪ.ግ የተሽከርካሪ ስም ጠቅሶ ትክክለኛ ያልሆነ የበር መውጫ ወረቀት አዘጋጅቶ 4ኛ የዐቃቤ ህግ ምስክር በሚያሽከረክረው ሲኖትራክ ተሽከርካሪ በማስጫን፤ 2ኛ ተከሳሽም ይህንን ብረት ሲጫን ቆሞ እየተቆጣጠር የነበረ እና ተሽከርካሪው ላይ የተጫነው የብረት መጠን የበር መውጫው ላይ ከተጻፈው የብረት መጠን

ከሙስና ምርመራ ... ወደ ገጽ 12 የዞረ

# ሳይቃጠል በቅጠል ...

ይደርጋል፡፡

እዚህ ላይ ግልጽ ሊሆን የሚገባው ህፃናት እስከ 10 ዓመታቸው ድረስ ስለሙስና ወንጀል እንዲያወቁ ሳይሆን ሥነምግባር ብቻ እንዲያወቁት ይደረግና ከ11 ዓመት በኋላ ግን የሥነምግባርና የሙስና መከላከል ሥልጠናዎችን እንዲወስዱ ይደረጋል፡፡

በአንዳንድ ሀገራት የተማከለ የፀረ-ሙስና ተቋማት አደረጃጀት ያላቸው ሲሆን፥ በክልሎች ቅርንጫፍ አደራጅተው ይንቀሳቀሳሉ፡፡ በፌደራል ፀረ-ሙስና ተቋም ውስጥ የክልል ፀረ-ሙስና ማስተባበሪያ ጽ/ቤት በማደራጀት ትግሉን በተማከለ አሰራር ይመራሉ፡፡ አንዳንድ ሀገራት ደግሞ ያልተማከለ አደረጃጀት በመከተል የፌዴራልና የክልል የፀረ-ሙስና ተቋማት ያላቸው ሲሆን ክልሎች የፌዴራል የሙስና መከላከል ስትራቴጂ መነሻነት የራሳቸውን የሙስና መከላከል ስትራቴጂ ነድፈው ይንቀሳቀሳሉ፡፡

ከፌዴራል ፀረ-ሙስና ተቋም ጋር ትይዩ የሆነ የፀረ-ሙስና ህጎችም አላቸው፡፡ ሀገራዊ የሙስና መከላከል ስትራቴጂ በጋራ ይገመግማሉ፥ አቅጣጫ ያስቀምጣሉ፡፡ ከሁለቱም አደረጃጀቶች የተሻለ ውጤታማ ሆነው እየታዩ ያሉት የተማከለ አደረጃጀትን ተከትለው የሚንቀሳቀሱ ሀገራት የፀረ-ሙስና ተቋማት መሆናቸውን መረጃዎች ያመለክታል፡፡

በፀረ-ሙስና ትግል ቀዳሚ ሚና ያላቸው የሲቪክ ማህበራት ናቸው፡፡ በኢስያ ሀገራት ውስጥ የሲቪክ ማህበራት የፀረ-ሙስና ተቋማት አመራሮች ሹመት ላይ ጭምር ሚና አለቸው፤ የፀረ-ሙስና ተቋም ተሿሚ የኃላ ታሪካቸው ላይ ሥነምግባር ችግር ለፀረ-ሙስና ተቋም በአመራርነት እንዳይቀርቡ አስተያየት ይሰጣሉ፤ በፀረ-ሙስና ትግል ላይ መንግስትን በትኩረት ይሞግታሉ፡፡ በሀገሪቱ ያለው የፀረ-ሙስና ትግል ላይ ሦስት ዓይነት ሚና ይወጣሉ።

የመጀመሪያ መንግስት የፀረ-ሙስና ተቋምን የሚመራበትንና የሚደግፍበትን ሁኔታ ይገምግማሉ፤ ሁለተኛ የፀረ-ሙስና ተቋም ራሱ በህግ የተሰጠውን ኃላፊነት በተገቢው ስለመወጣቱ ክትትልና ግምገማ ያካሂዳሉ፤ ይተቻሉ። በመጨረሻም ህብረተሰቡ ውስጥ ያሉ የሙስና ችግሮችን በጥናት በታገዘ መልኩ በመለየት ሙስና የሚጠየፍ ዜጋ ለማፍራት ይሰራሉ፡፡ ለፀረ ሙስና ትግል ወጣቱን ያነሳሳሉ፡፡

ከሲቪክ ማህበራት በተጨማሪ በፀረ-ሙስና ትግል ሚና ያላቸው ሚዲያዎች ናቸው፡፡ ሚዲያዎች በቅድሚያ ራሳቸውን ከሙስና ነፃና ገለልተኛ ያደርጋሉ፡፡ በመንግስት ተቋማት ውስጥ በኃላፊዎች የሚፈጸሙ የሙስና ቅሌቶችን በምርመራ ጋዜጣኝነት ሥራ እያነፈነፉ ለህዝብ ያጋልጣሉ፤ የተባለሹ አሠራሮች ከተገኙ እንዲስተካከሉ አብክረው ይሰራሉ፡፡

የመንግስት ተቋማት አመራርና ሠራተኞች ለሙስና ያላቸውን አመለካከትና የሥነምግባር ሁኔታ ላይ በየጊዜው በጥናት በመፈተሽ የሥነምግባር ሁኔታ እየቀነሰ ከመጣ ሙስና እንደጨመረ ይደመድሙታል፡፡ አንዳንድ ጊዜ መንገድ ላይ በጣም ውድ የሆኑ እቃዎችን በማስቀመጥና በስውር በመከታተል ያገኙትን ዕቃ ለራሳቸው ይወስዱታል ወይስ ለፖሊስ ሪፖርት ያደርጋሉ የሚለውን ፍተሻ በማካሄድ በሀገሪቱ ያለውን የሙስና ሁኔታ ላይ ውሳኔ ይሰጣሉ፡፡ በኢስያ ሀገራት ከ10 ሰው 9ኙ ሠው በመንገድ ላይ ያገኘውን ውድ ዕቃ ለባለቤቱ እንዲመለስ ለፖሊስ ሪፖርት ያደርጋሉ፡፡

ሌላው የፀረ-ሙስና ተቋማት በገለልተኝነትና ነፃነት ሁኔታ ነው፡፡

የተባበሩት መንግስታት የሙስና መከላከል ሥምምነት ሠነድ ላይ የፀረ-ሙስና ተቋማትን የሚመሩ ሰዎችን በተቋማት የተወሰኑ የጊዜ ገደብ የሚሾሙና ከማንኛውም ወገን ነፃና ገለልተኛ መሆን እንዳለባቸው (በሥነምግባር ጥሰት ወይም አቅም ማነስ ካልሆነ በስተቀር የህግ ከለላና በጊዜ ገደብ የሚሾሙ)፣ ለፀረ-ሙስና ተቋማት በቂ የሆነ በጀት እንዲመደብለት፤ ይህም በህግ አውጪ እንዲፈጸም፣ በሙያው ብቃትና ክህሎት ሠራተኞች በተሻለ ክፍያ ተቀጥረው ወይም ተመድበው እንዲሠሩ፣ ተቋሙ በመንግስት አካል ተጽዕኖ የማይደረግበት፣ ተጠያቂነት በትክክል የሚረጋገጥበት ተቋም መሆን እንዳለበት ያስቀመጣቸው ድንጋጌዎች አሉት፡፡

ሀገራችን የተባበሩት መንግስታትና የአፍሪካ ህብረት የሙስና መከላከል ስምምነትን ተቀብላ በአዋጁ 944/97 እና 945/97 አጽድቃለች፡፡ በአዋጅ ቁጥር 235/93 ለመጀመሪያ ጊዜ የፀረ-ሙስና ተቋም አቋቁማለች፡፡

በዚህ መሠረት ሁሉም ክልሎች የፀረ-ሙስና ተቋማት አቋቁመዋል፡፡ በፌዴራልና በክልል ተቋማት ውስጥ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች ተደርጅተዋል፡፡

የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ተጠሪነት እስከ 2014 ዓ/ም ድረስ ሁለት ጊዜ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሁለት ጊዜ ደግሞ ለጠቅላይ ሚኒስቴር ሆኗል፡፡ ለፀረ-ሙስና ተቋም የሚሾም ኮሚሽነር ለስድስት ዓመት ቆይታ የሚመደብ ቢሆንም ባለፉት ሃያ አንድ ዓመታት ከተመደቡት አምስት ኮሚሽነር በትክክል በአዋጅ የተሠጠውን ቆይታ ያጠነቀቁት አንድ ኮሚሽነር ብቻ ናቸው፡፡

የመጀመሪያው ኮሚሽነር አራት ዓመት ብቻ ቆይተው እንዲነሱ ሲደረግ፣ ሁለተኛው ኮሚሽነር በሁለት ዓመት ቆይታ ተነስተዋል፡፡ ሶስተኛው ኮሚሽነር በኃላፊነት የቆዩት አስራ ስምንት ወራት ነው፡፡

የክልል የፀረ-ሙስና ተቋማት አመራር ሹመት እንደፌዴራል በአዋጁ ላይ የቆይታ ጊዜ የተገደበ ቢሆንም በህጉ መሠረት ተፈፃሚ ሲሆን አይታይም፡፡

በፀረ-ሙስና ትግል ላይ በቂ እውቀትና በልምድ የካበተ፣ የፈጠራ ክህሎት ባለው፣ በተረጋጋና በጥቅልሉ በቂ ዕውቀትና ክህሎት እንዲሁም ሥነምግባር ባለው አመራር መመራት እንዳለበት አንዳንድ ፅሁፎች ይገልፃሉ፡፡ የፀረ-ሙስና ትግል ላይ የመንግስትና ህዝብ ጽኑ ፍላጎት ያለበት ተቋም ስለሆነ የሁለቱንም ፍላጎት አጣጥሞ መምራት የሚችለው የመንግስትንና የህዝብን ፍላጎት በትክክል በመረዳት በብቃትና ክሂሎት መምራት ሲቻል ነው፡፡

የፀረ-ሙስና ተቋማት የበጀት አፈቃቀድ ገለልተኝነትና ነፃነት ላይ ያተኮረ እንዲሆን የተባበሩት መንግስታት የፀረ-ሙስና ትግል የጃካርታ ስምምነት ይገልፃል፡፡ በዓለም ላይ ያሉ የፀረ-ሙስና ተቋማት በጀት የሚሰላውና የሚፈቀደው እንደዲሞክራሲ ተቋማት ነፃና ገለልተኛ በሆነ መልኩ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሲሆን፤ በሀገራችን የፀረ-ሙስና ተቋም የበጀት ጣሪያውን የሚወስነውና የሚገድበው የገንዘብ ሚኒስቴር ነው፡፡

ስለሆነም ኮሚሽኑን እንደማንኛውም ተቋም የተመደበለትን በጀት ብቻ በመጠቀም ሥራውን የሚያከናውን ከሆነ በሥራ ውጤታማነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ማሳዳሩ እንዳማይቀር ይገመታል፡፡

በሀገራችን የፀረ-ሙስና ተቋም አወቃቀር ከ1993 እስከ 2008 ዓ/ም ድረስ የሥነምግባር ትምህርት መስጠት፣ የሙስና መከላከል፣ የምርመራና ክስ ሥራዎችን ለመሥራት በሚችል ሁኔታ የተደራጀ ነበር፡፡ ክልሎችም በተመሳሳይ መልኩ የተዋቀሩ ነበሩ፡፡ በወቅቱም ተቋማቱ ለተለያዩ የማህበረሰብ አካላት የሥነምግባርና የሙስና መከላከል ትምህርት የመስጠት፣ በተቋማት ውስጥ የሙስና ሥጋት ቅነሳ ሥራዎችን መሥራት፣ የሀብት ማሳወቅና ምዝገባ ሥራዎችን ማከናወን፣ የሙስና ወንጀል ጥቆማዎችን በመቀበል፣ በመመርመርና በማስቀጣት የተመዘበረ ሀብት የማስመለስ ሥራዎች ተሰርቷል፡፡

ከ2009 ዓ/ም ጀምሮ ግን የሙስና ወንጀል የመመርመር፣ የማስቀጣትና የተመዘበረ ሀብት የማስመለስ ሥራዎችን ለፌዴራል ፖሊስና ለፍትህ ሚኒስቴር እንዲዛወር ተደርጓል፡፡ በወቅቱ ይህን ሥራ ለፍትህ አካላት ለማዛወር ምክንያት የተሰጠው የፍትህ አካላት ሥራዎችን ለህብረተሰቡ በተቀላጠፈ መልኩ የአንድ መስኮት አገልግሎት ለመስጠት እንዲያመች በሚል ነበር፡፡ የሙስና ወንጀል ጥቆማዎች በመቀበል የመመርመር ሥራዎች ለፌዴራል ፖሊስ ሲሰጥ፥ የሙስና ወንጀል ተጠርጣሪዎችን በመክሰስ የማስቀጣትና የተመዘበረ ሀብት የማስለመስ ሥራዎች ለፍትህ ሚኒስቴር ተሰጧል፡፡

በመሆኑም የፀረ-ሙስና ተቋማት ከህብረተሰቡ የሚገጥማቸው የሙስና መረጃ ጥቆማዎች ሲደርሳቸው ተቀብለው ለሁለቱም የፍትህ ዘርፍ ተቋማት በማቅረብ ተፈፃሚነት ላይ ክትትል ያደርጉበታል፡፡ የፌዴራሉ የፀረ-ሙስና ተቋም ከሁለቱም የፍትህ ተቋማት የሙስና ወንጀል መረጃዎችን በመቀበል ሀገራዊ የፀረ-ሙስና እንቅስቃሴ የሚያሳይ ሪፖርት እንዲያዘጋጅ ኃላፊነት ተሰጥቶታል፡፡

ሀገሪቱም የሙስና መከላከል ስምምነት በመፈረሟ የሙስና መከላከል፣ የሙስና ወንጀል የመመርመርና የማስቀጠት፣ የተመዘበረ ሀብት የማስመለስ፣ የሀብት የማሳወቅና የምዝገባ ሥራዎችን፣ መረጃዎችን በማደራጀትና ሪፖርት በማዘጋጀት በስምምነቱ መሠረት በሌሎች ስምምነቱን በፈረሙ ሀገራት አማካይነት ለማስገምገም መረጃዎችን ከፍትህ አካላት የማሰበሰብ፣ የማደራጀትና ሪፖርት የማዘጋጀት በመጨረሻም በማስገምገም ግብረመልስ መቀበልና በትግበራ መርሃ ግብር መሠረት ተግባራዊነትን የመከታተል ሥራ የፀረ-ሙስና ተቋም ይተገብራል፡፡

በሀገራችን የፀረ-ሙስና ትግል የሚካሄደው በፀረ-ሙስና ተቋም፣ በፌዴራል ፖሊስና በፍትህ ሚኒስቴር ተቋማት ሲሆን፥ ሶስቱም ከዜጎች የሚቀርቡ የሙስና ጥቆማዎችን በተነባበና በተዳመረ መልኩ በመቀበል በቅልጥፍና ውሳኔ የመስጠት አሰራር ጠንካራ ባለመሆኑ የሙስና ወንጀል ጥቆማዎች አቅርበው ወቅታዊ ምላሽ አይሰጠንም የሚሉ ወገኖች በርከታ ናቸው፡፡

ከላይ በተዘረዘሩት ተቋማት ታቅደው የሚከናወኑ ሥራዎችና ከህብረተሰቡ ፍላጎቶች ጋር አለመጣጣም ዋነኛው ችግር ነው፡፡ የፀረ-ሙስና ተቋማት የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም የሥነምግባር ሥልጠና ለተቋማት አመራርና ሠራተኞች በመስጠት ግንዛቤ ፈጥራናል ይላሉ፡፡ ነገር ግን በየዓመቱ ተመሳሳይ በሆኑ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ ሥልጠናዎችን በተደጋጋሚ ለተመሳሰይ ሰዎች የመስጠት፣ በትምህርት ደረጃቸው፣ በሙያቸውና በዕድሜ ለተለያዩ ሰዎች ተመሳሳይ ርዕስና መድረክ በማዘጋጀት ስልጠና የመስጠት፣ በየዓመቱ ሥልጠና ለመስጠት ተመሳሳይ ሥልጠና ሥልት መከተል፣ ለሥልጠና ጥራትና ተገቢነት የተረጋገጠ የማሰልጠኛ ማቴሪያል አለመጠቀም የመሳሰሉት ችግሮች ይስተዋልበታል፡፡ በሚዲያዎች የሚተላለፉ የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ስፖቶች፣ ጭውውቶችና ድራማዎች በራሳቸው ሙስና ለመሥራት ስልትን የሚያሳዩ ናቸው የሚሉ አንዳንድ ወገኖች አሉ፡፡

በተመልካች ዓይን ላይ በቀላሉ ሊገቡ የሚችሉ ሁል ጊዜ ለማስተወስ የሚያስችሉና ሳቢ የሆኑ መልዕክቶች ጥንቃቄ ተደርገው ስለማይዘጋጁ እምብዛም በሰው አእምሮ ውስጥ በቀላሉ የሚያዙ ባለመሆናቸው የህብረተሰቡን ፍላጎት የሚያረኩ ሆነው አልተገኙም፡፡

ሌላው የሙስና መከላከል ሥራ ነው፡፡

ኮሚሽኑ በተቋማት ውስጥ የሙስና እና ብልሹ አሠራር ችግሮችን የመከላከል ሥራን በጥናት ላይ ተመስርቶ ያከናውናል፡፡ ለዚህ ሥራ በፀረ-ሙስና ተቋማት ውስጥ በቂ ዕውቀትና ልምድ ያለው ባለሙያ አለመኖር እንደተጠበቀ ሆኖ ተቋማትም ሥራውን የሙስና ወንጀል ምርመራ አድርገው ስለሚወስዱ ለጥናት ተፈላጊ የሆኑ ሠነዶችን ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆን፣ ተቋማት ለተካሄደው ጥናት የተሰጠውን የማሻሻያ ሀሳቦችን ተቀብሎ ለመተግበር ምክንያቶችን በማብዛት ተግባራዊ አለማድረግ በስፋት የሚታዩ ችግሮች እንደነበሩ ጸሐፊው በጥልቀት ይረዳል፡፡ ስለሆነም በተቋማት ውስጥ ሙስና እና ብልሹ አሠራር እየተበረከተ እንጅ እየቀነሰ አይደለም፡፡

የሀብት ማሳወቅና ምዝገባ ሥራ አራት አንኳር ጉዳዮች (የሀብት ምዝገባ፣ የጥቅም ግጭት መከላከል፣ የተመዘገበ ሀብት ለህዝብ ይፋ ማድረግ እና የተመዘገበ ሀብት ትክክለኛነትን ማረጋገጥ) መተግበርን የሚጠይቅ ቢሆንም፥ ከሀብት ምዝገባ ባለፈ ሌሎችን ተግባራት በአግባቡ አልተተገበሩም፡፡

ስለሆነም የህዝብ ፍላጎትና የፀረ-ሙስና ተቋማት ፍላጎት አልተጣጣመም፡፡

በመሆኑም የተመዘገበው መረጃ በተደራጀ መልኩ ለህብረተሰብ ይፋ ባለመሆኑ በርካታ የህብረተሰብ ክፍሎች በሀብት ምዝገባ መረጃ ግልጽነት ላይ ተደጋጋሚ ጥያቄና ቅሬታ ሲያቀርቡ ይሰማል፡፡ በርግጥ የተመዘገበ ሀብት ትክክል ይሁን አይሁን በማጣራት እርምጃ የሚወሰድበት አግባብ ጠንካራ ባለመሆኑ አንዳንድ ሀብት አስመዝገቢዎች የሀብት መጠናቸውን የደብቁ ወይም ወደፊት በሙስና ሀብት ለማካበት ዕቅድ ያላቸው ሰዎች የሌላቸውን ሀብት እያስመዘገቡ መሆናቸውን ምልክቶች ይታያል፡፡

የፀረ-ሙስና ትግሉ ያለህብረተሰብ ንቁ ተሳትፎ የሚሳካ አይደለም፡፡ የፀረ-ሙስና ተቋማት ህብረተሰቡን በተደራጀ መልኩ ለማሳተፍ የሚያደርጉት ጥረቶች ቢኖሩም ሙስናን የሚጠየፍና የማይደግፍ ህብረተሰብ ከማብዛት አንፃር ገና ብዙ መሥራትን ይጠይቃል፡፡ ህብረተሰቡ በገቢ በሙስና የከበረውን ሰው ከየት አመጠህ ብሎ የመጠየቅ፣ ምንጩ ያልታወቀ ሀብት የሚያከብቱ ሰዎችን በማወቅ ለሚመለከተው አካል የመጠቆም፣ ሙስና በሀገር ላይ እና በዜጎች ላይ የሚያስከትለውን በመረዳት ጉቦ ባለመክፈል ወይም በመከላከል ሥራ ላይ በትጋት የመታገል ሁኔታዎች ደካማ ናቸው፡፡

በአንድ ወቅት ላይ የብልጽግና ፓርቲ አባላት ከፓርቲው ጉባኤ በኋላ ህዝቡን ሲያወያዩ ያነሱ ከነበሩት ችግሮች ውስጥ ሌብነት በጣም መንሳራፈቱ፤ ያለ ሌብነት አገልግሎት ማግኘት እየታቸለ አለመሆኑን፣ ጥቂት ግለሰቦች በሌብነት እየከበሩ መሆኑን በመግለጽ መንግስት ይህን ችግር ለመቅረፍ ትኩረት መስጠት እንዳለበት በአፅንዖት መግለፃቸው ይታወሳል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አህመድ (ዶ/ር) ሌብነት የእለት ተዕለት ችግር እየሆነ መምጣቱን እና ህግ ያስከብራሉ የተባሉ ፍርድ ቤቶች፣ ዓቃቤ ህግ፣ ፖሊስና ኦዲተር ወደ ሌብነት መግባታቸውን በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በግልጽ ገልፃዋል፡፡

በየተቋማት የሚገኙ የሥነምግባር መከታተያ ክፍል የሆኑ ሰዎች መካከል በተቋም ውስጥ ሙስና እንዲባባስ የሚያደርጉም እንዳሉ ጠቅላይ ሚኒስቴር ነግረውናል፡፡ መንግስት ሙስና ቀይ መስመር ነው ሲል ሙሰኞች ቀይ ምንጣፍ ማድረጋቸውን ገልፃዋል፡፡ ችግር መኖሩ በጣም ትክክልና እውነት ነው፡፡

በመንግስት ተቋማትና ህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ ሙስና እየተንሰራፋ ለመምጣት ምክንያቱ የአሰራር ህጎች ወቅታዊ አለመሆናቸው፣ በአሠራር ላይ የማጣራትና የማመዛዘን አሰራር አለመኖር፣ አለቃና የበታች ሠራተኛ ተባብረውና ተመካክረው ወደ ሌብነት እየገቡ መሆናቸው፣ የመንግስት ሠራተኛ የገቢ/የደመወዝ አነስተኛ መሆንና ኑሮውን በደመወዝ ብቻ ለመምራት ባለመቻሉ ወደ ሌብነት ፊቱን ማዞሩ፣ ሰውን በቀላሉ የሚያመልሉ ነገሮች መበረከታቸው የመሳሰሉት ሙስና ወይም ሌብነት ሥር እየሰደደ እንዲመጣ አድርጎታል፡፡

ሳይቃጠል በቅጠል ... ወደ ገጽ 12 የዞረ

# ሳይቃጠል በቅጠል ...

ስለዚህ ሙስናን ለመቀነስ ወደ ተቋማት በኃላፊነት የሚመደቡ ሰዎች በሥነምግባር የታነፁ ስለመሆናቸው ማረጋገጫ ስለማይወሰድ ወደ ኃላፊነት የሚመጡ አንዳንድ አመራሮች ሙስና እየተጠየፉ ያሉት በንግግር እንጅ በተግባር ግን የሉበትም።

ከባለሀብት ሀብት ጋር መዛመድ የሚፈልጉ የመንግስት ኃላፊዎች ብዙ ናቸው። ከባለሀብት ጋር የሚዝናኑና ቅንጡ ሆቴሎች ውስጥ የሚታዩ የመንግስት ባለሥልጣናት አሉ። በመሆኑም በአቋራጭ መበልጸግ የሚፈልጉ አቅራቢዎች ወይም አገልግሎት ሰጪዎች የመንግስት ኃላፊዎችንና አመራሮችን በተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞች ያማልላሉ።

የመንግስት አገልግሎት የሚሰጡ የመንግስት አመራርና ሠራተኞች ለሚሰጡት አገልግሎት አስገድደው ጉቦ ይቀበላሉ ወይም የአገልግሎት ፈላጊው ከመንግስት አገልግሎት ሰጪ ጋር በመመሳጠር ህገወጥ አገልግሎት ያገኛል። መንግስት ይህ ሁኔታ በስፋት ባለበት ሁኔታ ሙስናን ከሀገር ለመቀነስ ብሎም ለማስወገድ በጣም ይከብደዋል።

ስለሆነም ይህ ሥራ በገለልተኝነትና በነፃነት የሚሠሩ ተቋማትን ያለሥጋት ነፃ ሆነው እንዲሠሩ በማድረግ የሥራ ውጤታቸውን በአንክሮ መከታተልና መገምገም ብሎም ማገዝ ሙስናን ለመቀነስ ከፍተኛ ዕገዛ እንዳለው ሳይታለም የተፈታ ከመሆኑም በላይ በሙስና መከላከል ዙሪያ የተፃፉ ጽሁፎችም ይህን ይገልፃሉ።

በሥነምግባር የታነፁ የሚዲያ ጋዜጣኞችን በማሠመራት በየተቋማቱ ያሉ ሌቦችን የማጋለጥ ሥራ እንዲሠሩ ማበረታታት እና ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠርም ያስፈልጋል። ለውጤታማነቱ ደግሞ የተጠቀሱት ተቋማት ውስጥ ሥራቸውን ተመድበው ለሚሠሩ አመራሮችና ሠራተኞችም በሥነምግባር የታነፁና ሌብነትን የሚጠየፉ ሊሆን ይገባል።

መንግስት ሙስናን ለመቀነስ/ለመከላከል ያቋቋመው የፀረ-ሙስና ተቋም የሥነምግባር ግንባታና የሙስና መከላከል ሥራ በመሥራት ላይ እንደሚገኝ ይታወቃል። በተቋማት ውስጥም የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች በተቋማት ውስጥ ተደራጅተው ሙስና መከላከል ሥራ እንዲሠሩ ተደርጓል።

በየተቋማት ውስጥ የፋይናንስ እንቅስቃሴ ህግ፣ ደንብና መመሪያ ተከትሎ ማከናወኑን ለመከታተል ኦዲተር ተደርጅቷል። የፌዴራል ዋና ኦዲተር የተቋማት የበጀት አጠቃቀም ከፋይናንስ ህግ፣ ደንብና መመሪያ መሠረት ጥቅም ላይ ስለመዋሉ ያረጋግጣል። የእንባ ጠባቂ ተቋም በተቋማት አስተዳደራዊ በደል እንዳይደርስ ክትትልና ግምገማ ያካሄዳል። የፌዴራል ፖሊስና ፍትህ ሚኒስቴር የሙስና ወንጀል የመቀበል፣ የመመርመር፣ የማስቀጣትና የተመዘበረ ሀብት የማስመለስ ሥራ ይሰራል። ይህ ሁሉ ተቆጣጠሪ አካላት እያሉ ሌቦች የመንግስትን ሀብትና ንብረት ያለአግባብ ይሠርቃሉ፣ ይመዘብራሉ፣ ለምን? ዘላቂ መፍትሄ ይፈልጋል።

ስለዚህ መንግስት ለፀረ-ሙስና ትግል ፈርጣማ ጡንቻ ያለውና ጥርስ ያለው አንበሳ የሆነ ኃላፊነቱን በተገቢው መንገድ ሊወጣ የሚችል፥ ከየትኛውም ወገን ነፃና ገለልተኛ የሆነ የፀረ-ሙስና ተቋም በማደራጀት ተቋሙም ልዩ የሙያ ብቃትና ክህሎትን የሚጠይቅ ሥራን በቅልጥፍና ለማከናወን ጥራት ያለው አደረጃጀትና አሠራር በመፍጠር እንዲንቀሳቀስ ማድረግ፣ በሀገራችን ካለው የሙስና ወንጀል መበራከት አኳያ ሲታይ፤ ከአራት አማራጮች አንዱን መውሰድ ለችግሩ መፍትሄ ይኖረዋል የሚል ጸሐፊው አስተያየት አለው።

የመጀመሪያ አማራጭ የፀረ-ሙስና ተቋም ከሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ሥራ በተጨማሪ የሙስና ወንጀል ጥቆማዎችን የመቀበል፣ የመመርመር ኃላፊነት ተጨምሮለት መርምሯቸው የሚያቀርባቸውን የሙስና ወንጀል ላይ የመክሰስ፣ የማስቀጣትና የተመዘበረ ሀብት የማስመለስ ሥራ በፍትህ ሚኒስቴር እንዲሆን ማድረግ፣ ወይም

ሁለተኛ አማራጭ የፀረ-ሙስና ተቋም የሙስና ወንጀል ጥቆማዎችን የመቀበል፣ የመመርመር፣ የመክሰስ፣ የማስቀጠት እና የተመዘበ ሀብት የማስመለስ ሥራ እንዲሠራ ከማድረግ በተጨማሪ የሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ሥራን በትኩረት እንዲሠራና በጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ውስጥ የተቋሙን አፈፃፀም በየጊዜው የሚከታተልና የሚደግፍ ግብረ ኃይል ማደራጀት፣ ወይም

ሶስተኛአማራጭየፀረ-ሙስናተቋምከሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ሥራ በተጨማሪ በገንዘብ መጠን የተገደበ ከፍተኛ የሙስና ወንጀል ጥቆማዎችን የመቀበል፣ የመመርመር፣ የመክሰስ፣ የማስቀጣትና የተመዘበረ ሀብት የማስመለስ ሥራ እንዲሠራ ማድረግ፤ የፍትህ ሚኒስቴር በገንዘብ መጠን የተገደበ መካከለኛ የሙስና ወንጀል ጥቆማዎችን የመቀበል፣ የመመርመር፣ የመክሰስና የማስቀጠት፣ የተመዘበረ ሀብት የማስመለስ ሥራ እንዲሠራ፣ የፌዴራል ፖሊስ ደግሞ በገንዘብ መጠን የተገደበ ጥቃቅን የሙስና ወንጀል ጥቆማዎችን የመቀበልና የመመርመር ሥራዎችን በመሥራት የሚመረምሯቸውን ጉዳዮች ለፍትህ ሚኒስቴር እንዲያቀርብ ማድረግ እና ሶስቱን ተቋማት አፈፃፀም በየጊዜው የሚከታተልና የሚገምግም ግብረኃይል በጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ማደረጃት፣ ወይም

አራተኛ አማራጭ አሁን በሥራ ላይ ያለውን አደረጃጀት በሰው ኃይልና በቁሳቁስ አጠናክሮ ማስቀጠል፣ ወይም

አምስተኛ አማራጭ ለፀረ-ሙስና ተቋም ተጠሪ የሆነ የሙስና ወንጀል ጥቆማ መቀበያ፣ መመርመሪያ ኢንስቲትዩት ማደረጃት፣ በኢንስቲትዩቱ ተመርምረው የተጠናቀቁ ጉዳዮች በፍትህ ሚኒስቴር ለሙስና ወንጀል ክስ ራሱን የቻለ ዐቃቤ ህግ በማደራጀት በየጊዜው ከዜጎች የሚቀርቡ ሁሉንም ዓይነት የሙስና ወንጀል ጥቆማዎች ሳይባክኑ እንዲከሰስ፣ የሙስና ወንጀል ተጠርጣሪዎች ተገቢውን ቅጣት እንዲቀጡ፣ የተመዘበረ የህዝብና የመንግስት ሀብት እንዲያስመለስ ማድረግ ሲሆን፤ ከሶስቱም አማራጮች የተሻለውን በጥናት በመወሰን መተግባር በተቋማት ውስጥ ተገልጋይ ህብረተሰብን ለማንገላታት፣ ለማጉላለትና ምልጃ ለመጠየቅ የተዘረጉ አሠራሮችንና አደረጃጀቶችን በማስወገድ እንዲሁም የህዝብና የመንግስት ሀብትና ንብረት ከምዝበራ በማዳን በመንግስት አገልግሎት ላይ የህብረተሰብ እርካታን ማሳደግ የታለማውና የተነደፈው የብልጽግና ጉዞ እውን ይሆናል የሚል እምነት አለን።

# ከሙስና ምርመራ ዘገባ ማህደር ...

ብልጫ እንዳለው እያወቀ እንዲሁም በመውጫ ላይ የተጻፈው መረጃ ሀሰተኛ መሆኑን እያወቀ አጃቢ በመሆን ተሽከርካሪ ውስጥ በመግባት ከግቢ ሊወጡ ሲሉ የበር መውጫ ሲጠየቁ ያቀረቡት ሰነድ ሀሰተኛ የበር መውጫ መሆኑ በመረጋገጡ በቁጥጥር ስር የዋሉ በመሆኑ ተከሳሾች በፈፀሙት በሥራ ተግባር የሚፈጸም የመውሰድና መሰወር ከባድ የሙስና ወንጀል ዐቃቤ ህግ ክስ መስርቶባቸዋል።

በዚህም መሰረት 1ኛ ተከሳሽ በችሎት ቀርቦ ክሱ ተነቦለታል። ጉዳዩን የተመለከተው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 5ኛ የሙስና ወንጀል ጉዳዮች ችሎትም 1ኛ ተከሳሽ በቀረበበት ክስ ላይ የሚያቀርበውን የክስ መቃወሚያ እና የ2ኛ ተከሳሽን መቅረብ ለመጠባበቅ ለሚያዚያ 12 ቀን 2015 ዓ.ም ቀጠሮ መሰጠቱን የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

ሌላው በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፍትህ ሚኒስቴር የጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ዘርፍ የሙስና ወንጀል ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጀኔራል ዐቃቤ ህግ ከመንግስት በህገ-ወጥ መንገድ ከ33 ሚሊዮን ብር በላይ ካሳ እንዲሁም የሊዝ ግምቱ ከ58 ሚሊዮን ብር በላይ የሆነ ምትክ ቦታ በወሰዱና እንዲወሰድ አድርገዋል በተባሉ በ39 የየካ ክ/ከተማ መሬት አስተዳደር ሰራተኞችና በ15 የአርሶ አደር ኮሚቴዎች እንዲሁም ተጠቃሚ በሆኑት በ30 ግለሰቦች በአጠቃላይ በ85 ግለሰቦች ላይ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የልደታ ምድብ የሙስና ወንጀል ችሎት ሥልጣንን አላግባብ መገልገል ከባድ የሙስና ወንጀል ክስ መመስረቱ ተመላክቷል።

ተከሳሾች በ1996 ዓ.ም የወጣውን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1) (ሀ)፣33 እና የሙስና ወንጀሎችን ለመደንገግ የወጣውን አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 9 (1) (ሀ) (ለ) እና (2) ስር የተመለከተውን ድንጋጌ በመተላለፍ ወንጀሉን ፈጽመዋል በሚል ክስ ተመስርቷል።

እንደ ምክትል ዳይሬክተር ጀኔራሉ ገለጻ 39ኙ የየካ ክ/ከተማ መሬት አስተዳደር ሰራተኞች በተለያየ የስራ ሃላፊነት ላይ፤ እንዲሁም 15ቱ ተከሳሾች የአርሶ አደር ኮሚቴ አባላት ሆነው ሲሰሩ በልማት ምክንያት ለሚነሱ ባለይዞታዎች የሚሰጥ የካሳና ምትክ መሬት አሰጣጥ ሂደትን ተገን በማድረግ አርሶ አደር ያልሆኑ በልማት ምክንያትም ከይዞታቸው ያልተነሱ 30 ለሆኑት ተከሳሽ ግለሰቦች አርሶ አደር እንደሆኑና በልማት ምክንያት እንደተነሱ በማስመሰል በአዲስ አበባ ከተማ ከፍተኛ ዋጋ ሊያወጡ በሚችሉ በቸርችል ጎዳና፣ በመገናኛና ካራ ኤሎ አካባቢዎች ላይ የሊዝ ዋጋ ግምቱ ከ58ሚሊዮን ብር በላይ የሚሆን መሬት በህገ-ወጥ መንገድ በምትክነት እንዲወስዱ በተቀናጀ አካሔድ መስራታቸውን መረጃው ያሳያል።

በተጨማሪም የአዲስ አበባ ውሀና ፍሳሽ ባለስልጣን ከ2010 ዓ/ም እስከ 2014 ዓ/ም ድረስ በሰራው የለገዳዲ ፌዝ 2 የውሀ ልማት ፕሮጀክት ምክንያት የልማት ተነሺዎችን እያስተናገደ በነበረበት ወቅት ቀኑ እና ወሩ በውል ባልታወቀ በ2012 ዓ/ም እና 2013 ዓ/ም ላይ የአርሶ አደር ኮሚቴዎች የነበሩት 15ቱ ተከሳሾች ለ31ዱ ተከሳሽ ተጠቃሚ ግለሰቦች የአካባቢው ነዋሪና አርሶ አደር ባልሆኑበት አግባብ አርሶ አደር ናቸው በሚል ሀሰተኛ ቃለ-ጉባኤ በማቅረብ፣ ከየካ ክ/ከተማ መሬት አስተዳደር ሰራተኞች ጋር በመሆን ለህዝብ ጥቅም ሲባል በሚለቀቅ መሬት ላይ ለሰፈረ ንብረት ስለሚከፈል ካሳና ምትክ ቦታ አሰጣጥ በተሻሻለው የአፈጻጸም መመሪያ መሰረት አግባብ ባለው አካል ሳይፈቀድ እንዲሁም ሌሎች እነዚህን ተግባራት ለመከወን የወጡትን መመሪያዎች በመጣስ ወደ ቦታው ወርደው በእርግጥም በልማቱ ምክንያት ከይዞታቸው የሚነሱና የሚፈርስ ቤት ያላቸው መሆኑን ሳያረጋግጡ እና መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች በአግባቡ ባልተሟሉበት ሁኔታ ለ31ዱ ተጠቃሚ ተከሳሽ ግለሰቦች በሌሎች ሰዎች ይዞታ ላይ በህገ-ወጥ መልኩ የይዞታ ማህደር ተደራጅቶ መብት ከተፈጠረላቸው ይዞታዎች ላይ በልማቱ ምክንያት እንደተነሱ በማስመሰል ህገ-ወጥ የካሳ ማህደሮችን የማደራጀት ስራ በመቀናጀት መስራታቸውን ተመላክቷል።

በአጠቃላይ የየካ ክፍለ ከተማ የመሬት አስተዳደር ሰራተኞችና የአርሶ አደር ኮሚቴዎቹ 30 ለሆኑት ተጠቃሚ ግለሰቦች በተጭበረበረ መልኩ በ13,990 (አስራ ሶስት ሺህ ዘጠኝ መቶ ዘጠና) ካሬ ሜትር መሬት ላይ ህገ-ወጥ መብት በመፍጠርና የልማት ተነሽ እንደሆኑ በማስመሰል የካሳ ማህደሮችን አደራጅተው የህዝብና የመንግስት ሀብት የሆነውን በአዲስ አበባ ከተማ ከላይ በተጠቀሱት አካባቢዎች አጠቃላይ የሊዝ ዋጋ ግምቱ 58,601,735 ብር የሚያወጣ ቦታ በህገ-ወጥ መንገድ እንዲወስዱ እና 33,013,572.00 (ሰላሳ ሶስት ሚልየን አስራ ሶስት ሽህ አምስት መቶ ሰባ ሁለት) ብር የካሳ ገንዘብ እንዲሰራ በማድረጋቸው ሁሉም ተከሳሾች በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን በፈፀሙት ሥልጣንን አላግባብ መገልገል ከባድ የሙስና ወንጀል መከሰሳቸውን ተጠቁሟል። ሌሎች ተጠርጣሪዎችን በተመለከተም ምርምራዉ እንደቀጠለ ነው።

ጉዳዩን የተመለከተው ችሎትም የቀረቡትን ተከሳሾች የክስ መቃወሚያ ቀጠሮ የያዘ ሲሆን፤ ፖሊስ ያልቀረቡትን ተከሳሾች እንዲያቀርብ ትዕዛዝ መሰጠቱን ከፍትህ ሚኒስቴር የተገኘው መረጃ ያስረዳል።

በሌላ የሙስና መረጃ በቂርቆስ ክ/ከተማ የአነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅርጫፍ ጽ/ቤት የአወሳሰን ባለሙያ የሆነው የሺጥላ ሻውል የቅርጫፍ ጽ/ቤቱ ግብር ከፋይ የሆኑ ግለሰብን ካቀረብሽው 10 ደረሰኞች መካከል 8ቱ የተበላሹ በመሆኑ ወደ አጣሪ ኮሚቴ መላኩንና ሁለቱ ደግሞ እጄ ላይ ይገኛሉ በማለት ጉዳዩን ለማዳፈን ግን 100ሺ ብር ጉቦ እንዲሰጠው ይጠይቃል።

የግል ተበዳይ ያቀረቧቸው ሰነዶች ትክክለኛ እንደሆኑ ለማስረዳት ቢሞክሩም ባለሙያው ሳይቀበላቸው ይቀራል።

የአወሳሰን ባለሙያ የሆነው ይህው ግለሰብ በቢሮ ስልክ ደጋግሞ በመደወል የግል ተበዳይን በማስጨነቅ በህግ እንደሚጠየቁ በማስፈራራት 70ሺ ብር ለመቀበል ይስማማል።

የግል ተበዳይ ጉዳዩን ለተቋሙ ኃላፊዎች በማሳወቅ በቂርቆስ ክፍለ ከተማ የደንበል አካባቢ ፖሊስ ጣቢያ ባደረገው ክትትል በቅርጫፍ ፅ/ቤቱ የአወሳሳን ባለሙያ የሆነው ሙያተኛ 22 አካባቢ ከሚገኘው መስቲ ሬስቶራንት አካባቢ መጋቢት 13 ቀን 2015 ዓ/ም ገንዘቡን ሲቀበል እጅ ከፍንጅ መያዙን እና የዚህ ወንጀል ተባባሪ የሆነው በተቋሙ የጥቆማ አቀባበል ባለሙያ ከፍተኛ ኦፊሰር የሆነው ግዛቸው ውዴ ደግሞ በተመሳሳይ ቀን በጉቦ የተገኘውን ገንዘብ ሲቀበል መገናኛ አካባቢ እንደተያዘ ተመላክቷል።

ማህበረሰቡ መሰል ወንጀል ፈፃሚዎችን ለህግ አካላት አጋልጦ የመስጠት ልምዱ ይበል የሚያሰኝ ተግባር መሆኑን የአዲስ አበባ ፖሊስ እየገለፀ ወደፊትም የህዝብን እና የመንግስትን እምነት በማጉደል በማህበረሰቡ ላይ በደል የሚፈጽሙ አካላትን ወደ ህግ ለማቅረብ የሚደረገው እንቅስቃሴ ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል።

# ኪነ-ጥበብ

## እርቋል አትበሉ!

እርቋል አትበሉ!

ጉልበትና ስልጣን ጊዜ የሰጣችሁ፣ ነዋይና ንብረት በእጅ የጨበጣችሁ፡፡
በከንቱ አትመኩ ዓለም ኃላፊ ነች፣ ፅዋዋ ሲሞላ ጊዜ ትዞራለች፡፡
ጊዜ አለን ብላችሁ ህዝብ ስትበድሉ፣ ደጉን በተዝህሮ ሰው ስትበቀሉ፣
ፈጣሪ አያየነም እርቋል አትበሉ፡፡
ሰው ያለ ኃጢአቱ፣ ስታስሩ ስትፈቱ፣ በራሳችሁ ዳኛ በሙግት ስትረቱ፣
ገርፋችሁ በአለንጋ ፀጉር ስትሸልቱ፣ ‘’ንቀትል’’ ብላችሁ ስታሰናብቱ፡፡
ፈጣሪ አያየነም እርቋል አትበሉ፣ መርምሮ ያየዋል ስራችሁን ሁሉ፡፡
ሥልጣን እንደ ስኳር ማሩን ተመስላ፣ ዛሬ ብትጣፍጥ እንደ ፍሬ ሰግላ፣
ጥላ ትጠፋለች ጊዜዋ ሲሞላ፡፡
ልባችሁ ተሞልቶ በከንቱ ትዕቢት፣ በተንኮል በቅንዓት በምቀኝነት፣
ሰውን ብታጠፉ በጊዜ ሂደት፡፡
ግፍ እንዲሁ አይቀርም የማታ የማታ፣ በዚህ በዚያ ብሎ ይበቀላል ጌታ፡፡

ስልክ፡ 9555

አጭር የፅሁፍ መልዕክት፡ 9555

ድረ ገፅ፡ http://www.9555pmo.et/

ኢሜይል፡ http://9555pmo.et/

ቴሌግራም፡https://t.me/PMOfeedback

የሙስናና ብልሹ አሰራር ድርጊቶችን በጥቆማ መስጫ አድራሻዎች ያጋልጡ፣ይጠቁሙ!!

# መልካም ዜጋ

# የቅን ሰው መለኪያ ሚዛን

**ከድር ጀማል**

የተራበ ሆድ፤ ባዶ ቦርሳና የተሰበረ ልብ ህይወት ምን እንደሆነ ታስተምርሃለች፥ ሳዲዮ ማኒ ሰዎችን በቁመናቸው፣ በውበታቸውና ባላቸው የሀብት መጠን አትመዝናቸው፤ ሰዎችን በሚናገሩት ልክ ጥሩ፣ ሳቢ፣ መሳጭና ልብ የሚገዛ ንግግር ብቻ ልታምናቸው አይገባም:: ምክንያቱም በሚጣፍጠው ምላሳቸው የሚጎመዝዝ ሬት በልባቸው ውስጥ ሊኖር ይችላል:: ሰዎችን መመዘን ያለባቸው በሚናገሩት ንግግር ሳይሆን በሚፈጽሙት ተግባራቸው መሆን አለበት:: ምክንያቱም የሰው ልጅ ትልቁ መለኪያ መሆን ያለበት የገባውን ቃል በታማኝነት ጠበቆ መፈጸም ሲችል ብቻ ነው:: ከነዚህ ቅንና ቃል ጠባቂ ሰዎች መካከል አንዱ የመልካም ሥነምግባር ተምሳሌት የሆነው ሳዲዮ ማኒ (Sadio Mane) ይጠቀሳል::

የዚህ ጽሑፍ ዋና ዓላማ በዓለም አቀፍ ደረጃ ምርጥ የእግር ኳስ ኮከብ ተጫዋቾች ስለሆነው ሳዲዮ ማኒ የኳስ ጥበብና ችሎታ በዝርዝር ለመናገር ሳይሆን ተጫዋቹ ቅንነትን በመላበስ፥ የገባውን ቃል በመጠበቅ የሚያደርገውን ሰብዓዊነት የተሟላበት የመልካም ዜጋ ተግባር ለሌሎች ለማካፈል ነው::

ማኒ በባዶ ሆዱና በባዶ እግሩ፣ በባዶ የኪስ ቦርሳና በተሰበረ ልብ ውስጥ ያደገ ሰው ነው፤ ሆኖም የደረሰበትን ችግርና መከራ አልሰበረውም፥ እንዲያውም ይበልጥ እንዲጠነክርና ችግሮችን ተጋፍጦ እንዲወጣ ትምህርት ሆኖታል::

ማኒ በደቡብ ሴኔጋል ውስጥ ባለች ባባሊ (Bambali) በምትባል አንዲት ትንሽ መንደር ውስጥ እ.ኤ.አ. 10 April 1992 ተወለደ:: ቤተሰቦቹ በጣም በድህነት ውስጥ ከመኖራቸው ባለፈ በቤተሰቡ ውስጥ ያሉትን ልጆች መመገብ የሚያስችል አቅም ወይም ገቢ የሌላቸው በመሆኑ ማኒ ወደ አጎቱ ቤት በመሄድ እንዲኖር ተደረገ::

የማኒ አጎት ኑሮም ቢሆን በወቅቱ ከእጅ ወደ አፍ ብቻ በመሆኑ ወደ ትምህርት ቤት ልኮ ለማስተማር የሚያስችል አቅም አልነበረውም፤ በዚህም የተነሳ የማኒ መኖሪያና መዋያ ሥፍራ በመንገድ ላይ የእግር ኳስ የመጫወቻ ሜዳ ሆነ:: የእሱ በዚያች ገጠራማ መንደር ውስጥ የምትገኝ አቧራማ የእግር ኳስ መጫወቻ ሥፍራ የየዕለት መዋያው ሆነች:: መደበኛ ትምህርት ስለማይማር ጠዋት ከእንቅልፉ እንደነቃ ሮጦ ወጥቶ ማታ ፀሐይ ስትገባ ሲጫወት ውሎ ወደ ቤት ይመለሳል::

በህይወቱ የሚወደውና መሆን የሚፈልገው ነገር ቢኖር በዓለም አቀፍ ደረጃ ፕሮፌሽናል የእግር ኳስ ተጫዋች ሆኖ ራሱንና ሀገሩን በውድድር መድረክ አሸንፎ ማስጠራት ነበር:: ይህ ውስጣዊ ፍላጎቱ እንደ እሳተ ጎመራ እየተቀጣጠለ መጣ:: ይህ ውስጣዊ ፍላጎት ይበልጥ እንዲጎመራ ያደረገው ደግሞ የሴኔጋል ብሔራዊ ቡድን በዓለም ዋንጫ ውድድር ላይ በምድቡ ውስጥ የነበረችውን የዓለም ሻምፒዮን ፈረንሳይን በማሸነፍ ግማሽ ፍጻሜ በመድረሷ ነው::

ይህን ውጤት ሀገሩ በመገኘቷ የተነሳ እግር ኳስን አጥብቆ መሥራት ጀመረ፤ የእግር ኳስ ፍቅሩን በጣም እያየለ መጣ:: ይሁን እንጂ የሳድዮ ማኒ የእግር ኳስ ፍቅር ማየሉን የታዘቡ ቤተሰቦቹ ኳስ መጫወቱን እንዲተው ለማድረግ የተለያዩ የሥራ ዕቅዶች በማወጣት ተግባራዊ ለማድረግ ቢሞክሩም እሱ ግን አሻፈረኝ ብሎ ጨዋታውን ቀጠለ::

ቤተሰቦቹ የልጁ ሁኔታ ስላላማራቸው ጨዋታውን ከመከልከል ይልቅ መደገፉ ይሻላል በማለት ድጋፍ ያደርጉለትም ጀመር፤ ከዚያም የእርሻ ምርታቸውን በማሳደግ ባገኙት ገቢ ዳካር ውስጥ በሚገኝ Generation Foot, a football academy in Dakar በሚባል የእግር ኳስ ማሰልጠኛ አካዳሚ ውስጥ እንደገባና ስልጠና እንዲወስድ ይበልጥ ድጋፍ አደርገውለታል::



ይህን መነሻ በማድረግ ከብዙ ውጣ ውረዶች በኃላ ሳዲዮ ማኒ እ.ኤ.አ. 2016 በክረምት ዝውውር ወቅት ከሳውዝአምፕተን ዝውውር ለአምስት ዓመት ኮንትራት ፈርሞ በ34 ሚሊየን ፓውንድ ወደ ሊቨርፑልን ሲቀላቀል ከአፍሪካ እግር ኳስ ተጫዋቾች መካከል ውዱና ከፍተኛ ክፍያ የሚከፈለው ተጨዋች ሆኖ ነበር::

ይህ ብርቅዬ ሴኔጋላዊ አጥቂ ሳዲዮ ማኔ በዓመት እስከ አስር ሚልየን ዶላር ያህል ገቢ ያገኛል። የቀድሞ ህይወቱን በተመለከተ ጋዜጠኞች ሲጠይቁት በራስ መተማመንና በቅንነት የህይወት ገጠመኙን ያካፍላል::

በአንድ ወቅት ጋዜጠኞች ስለ ህይወት ታሪኩ ላቀረቡለት ጥያቄ ሲመልስ፥ "ርቦኝ ያውቃል፣ በክሰል ማውጫ ውስጥ ሰርቼ አውቃለሁ፣ ጫማ አጥቼ በባዶ እግሬም እግር ኳስን ተጫውቻለሁ፥ እናም አሁን ህዝቤን መርዳት እችላለሁ። ትምህርት ቤት መገንባትን እመርጣለሁ፣ ለተራቡት ባበላ፣ ለታረዙት ባለብስ ከፍተኛ የሆነ ውስጣዊ እርካታ ይሰማኛል:: በሀገሬ ሴኒጋል ስታዲየም፣ ትምህርት ቤት ገንብቻለሁ፤ በዛም ላሉ ደሃ ቤተሰቦች ሁሉ በየወሩ 70 ዩሮ እንዲደርሳቸው አደርጋለሁ፤ ለኔ ውድ መኪና፣ የቅንጦት ቤት፣ የግል አይሮፕላን ምንም አያደርግልኝም። ፈጣሪ ከሰጠኝ ጸጋ፣ ጥቂትም ቢሆን ለህዝቤ ባካፍል መንፈሳዊ እርካታ ይሰጠኛል::"

**ሰዎችን በሚናገሩት ልክ ጥሩ፣ ሳቢ፣ መሳጭና ልብ የሚገዛ ንግግር ብቻ ልታምናቸው አይገባም:: ምክንያቱም በሚጣፍጠው ምላሳቸው የሚጎመዝዝ ሬት በልባቸው ውስጥ ሊኖር ይችላል:: ሰዎችን መመዘን ያለባቸው በሚናገሩት ንግግር ሳይሆን በሚፈጽሙት ተግባራቸው መሆን አለበት**

"ቤተሰቦቼ በድህነት ውስጥ የሚኖሩ ነበሩ፤ እግር ኳስ ለመጫወት እንድችል እንኳን አንድ ጥንድ ጫማ ለመግዛት የሚያበቃ አቅም አልነበራቸውም:: እናቴ እኔንና ወንድሞቼን ለመመገብ ስትል የመንደሩ ሰዎች ልብስ ታጥብ ነበር፤ በዚህም የተነሳ ከህይወት ጋር ትግል የገጠሙ ህጻናትን ስመለከት ለመርዳት ውስጤ በከፍተኛ ደረጃ ይነሳሳል ምክንያቱም ያለፈውን ህይወቴን ያስታውሰኛል::" በማለት የመልካም ዜጋ ተምሳሌትነትን በተግባር አሳይቷል::

ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ፈረንሳይ በባቡር ስጓዝ ለእናቴ ለመደወል ፈልጌ ገንዘብ ስላልነበረኝ መደወል አልቻልኩም ነበር፤ ነገር ግን በቀጣዩ ቀን እዚያ ያሉ ጎደኞቼ ጋር በመሄድ ለስልክ መደወያ የሚሆን ገንዘብ እንዲሰጡኝ ጠይቄ ለእናቴ ደወልኩላት:: እናቴ አሁን ፈረንሳይ ነው ያለሁት አልኳት፥ የትኛው ፈረንሳይ? ብላ ጠየቀችኝ:: የኔን ፈረንሳይ ውስጥ መገኘት በፍጹም ልታምን አልቻለችም:: ፈረንሳይ አውሮፓ ነዋ! አልኳት:: አውሮፓ ምንድነው? አንተ አሁን የምትኖረው ሴኔጋል ውስጥ አይደለ እንዴ? በማለት ጠየቀችኝ:: አይደለም አሁን የምገኘው ፈረንሳይ ውስጥ ነው ብዬ መለስኩላት::

በጣም ተገረመች፤ ልታምን አልቻለችም:: ከዚያ በኃላም ቢሆን ነገሩን ለማረጋገጥ በተደጋጋሚ በየቀኑ ትደውልልኝ ነበር:: ሙሉ በመሉ ልታምን የቻለችው በቴሌቪዥን ስትመለከተኝ ነው:: ፕሮፌሽናል የእግር ኳስ ተጨዋች የመሆን ህልሜ በመጨረሻ በማሳካቴ ደስታዋ ወደር አልነበረውም:: ሆኖም ይህን ግብ ለማሳካት ጠንክሮ መስራት፥ ማንኛውም መስዋዕትነት ለመክፈል ዝግጁ መሆን፣ ለሙያ ሥነምግባር መገዛት አስፈላጊ ነገሮች ናቸው፤ በዓለም ላይ ከውስጣዊ ሰላም የበለጠ ሀብት የለም፥ በማለት አስተያየቱን ሰጥቷል::

በአጠቃላይ ይህ ያለ አባት ያደገው አፍሪካዊ ብርቱ ልበ ቀና ወጣት በልጅነቱ እጅግ አሳዛኝ የህይወት መሰናክሎች ቢያሳልፍም በመጨረሻ ቅንነትነት በመላበስ፥ ችግሮቹን በትዕግስትና በቆራጥነት በመሰባበር ለሌሎች የሀገሪቱ ዜጎች የመልካም ዜጋ ተምሳሌት በመሆን አገራዊ ግዴታውን በመወጣት ላይ ይገኛል::